# የኢትዮጵያ የፖለቲካ ቀውስ መንስኤና መፍትሄ በኔ እይታ

ማህደር 12-25-17

ግፍ፣ ድህነት፣ጭቆና እና አድልዎ የበዛበት ህዝብ የትግል ምቹ መደላደል ይሆናል፡፡ ለውጥ እናመጣለን፣ከችግርህ እናላቅቅሃለን፣ የተሻለ የብልፅግና መንገድ እናሳይሃለን፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንገነባልሃለን ለሚሉ የተለያዩ የፖለቲካ አቋም ለሚያንፀባርቁ የፖለቲካ ድርጅቶች እድል ሰጥቶ እንዲያድጉ፣ እንዲታገሉ እና ውጤት እንዲያሳዮት እድል ይሰጣል፡፡




በኢትዮጵያ ለዘመናት የጭቆና ቀንበር ተጭኗቸው የነበሩ ህዝቦች በተለያየ ወቅት የነበራቸውን ቁጣ ሲገልፁ ቆይተዋል፡፡ በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ ቁጣውን በትግልና በትእግስት ሲያሳይ ቆይቷል፡፡ በዚህ አጭር የግምገማ ሃተታየ ስለ ትግራይ ህዝብ ታሪክ ለመፃፍ ሳይሆን ከ1966 ዓ.ም ከአፂ ሃ/ስላሴ ስርዓት መገርሰስ ጀምሮ በኢትዮጲያ ፖለቲካ፣ የትግራይ ህዝብ ተሳትፎ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ፣ አሁን ያለውን ቀውስ ከነመፍትሄው እንዲሁም በህውሓት የትግል አካሄድ ላይ ያለኝን አተያይ፣ግጭት፣ ቁርኝትና ውጤት ላይ አስተያየቴን ለማንፀባረቅ ነው፡፡

እንደሚታወቀው በ1966 ዓ.ም የአፂ ሃ/ስላሴ መንግስት ከስልጣን በህዝብ ዓመፅ ሲወገድ የተፈጠረውን የስልጣን ክፍተት ተጠቅሞ የደርግ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ተቋቋሞ ለ17 ዓመታት ስልጣን ላይ ቆየ፡፡

ደርግ ስልጣን ለመያዝ ከማሰቡ በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ከኢህአፓ፣ኦነግ እንዲሁም የሲዳማ አርነት ንቅናቄ ከመሳሰሉት የተወሰኑ የፖለቲካ አደረጃጀቶች በስተቀር ጎላ ብሎ የሚታይ እና እጩ የስልጣን ተቀናቃኝ አልነበረም፡፡ ህዝቡ የጨቆነውን ስርዓት በነቂስ ወጥቶ በሚታገልበት ወቅት የህዝብ ጫና እና አመፅ የፈጠረው የፖለቲካ ግለት የፈጠራቸው አደረጃጀቶች እንጅ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታ ገምግመው እና ተረድተው የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች አልነበሩም፡፡

አንዳንዶቹ በተለይም ኦነግ እናኦብነግም ቢሆኑ በጠባብ ፖለቲካዊ መሰረት ላይ ያተኮሩ እና የህዝባቸውን እውነተኛ እውቀት መሰረት ያደረጉ ሳይሆኑ የኦሮሞ እና የሶማሊ ህዝቦች ይደርስባቸው የነበረውን ብሄራዊና መደባዊ ጭቆና በቅጡ ሳይመረምሩ ነገር ግን በወቅቱ ከነበረው አገዛዝ በመሸሽ ብቻ ችግሩ ይፈታል ብለው በማሰብ የተደራጁ ነበሩ፡፡

በተለይ ኦነግ በታሪክ እንደ አንድ አገርም ይሁን መስተዳድር ተዳድሮ የማያወቅን ሰፊ መልክአ ምድራዊ አሰፋፈር የያዘን ህዝብ አንድ አድርጎ የጋራ ስነልቦና ፈጥሮ እንዲሁም እጅግ ኋላቀር በሆነው የፊውዳል ስርዓት "በቅኝ" እንደተገዛ አሳምኖ ወደሚፈልገው የስልጣን ዙፋን ለመምጣት አዳጋች የሆነውን አቀበት ነበር የመረጠው፡፡

በመሆኑም ቀደም ብለው የተመሰረቱት ኦነግ፣ኢህአፓ እና ኦብነግ(OLF, EPRP & ONLF) ይሆኑ ቀጥለው የተመሰረቱት ሌሎች የፖለቲካ አደረጃጀቶች እንታገልልሃለን የሚሉትን ህዝብ መረዳት እና ለገጠመው ጭቆና መፍትሄ የማግኛ ትግል በቅጡ መቀየስ የሚያስችል ፖለቲካዊ እውቀትና ቁርጠኝነት ያልነበራቸው ነበሩ፡፡

ነገር ግን አብዛኞቹ ከነበራቸው ስሜታዊነት ባመዘነበት የፖቲካ እውቀት እና በውስጣቸው ከነበረ ቁጣ በስተቀር ኢትዮጵያን እና ህዝቦችዋን በህዝባዊነት እና በእኩልነት የገመገሙ አልነበሩም ፡፡ በወቅቱ ከህዝቡ ከተነሳው ግብታዊ አብዮት የተሻለ ስርዓት መገንባት የሚያስችል ሳይንሳዊ ግምገማ እና ትንተና በማድረግ የተገኙ አደረጃጀቶች አልነበሩም፡፡ በመሆኑም ነው ከሁሉም አደረጃጀቶች ለየት ባለ መንገድ ማለትም ስሜታዊነቱ እና ግብታዊነቱ እንዳለ ሆኖ ነገር ግን በወታደራዊ ዲስፕሊን እና በጦር መሳርያ ራሱን አደራጅቶ የነበረው የወታደራዊው ክፍል ለስልጣት ራሱን ያጨው እና በቀላሉ ስልጣን ሊቆናጠጥ የቻለው፡፡

የወታደራዊው መንግስት መሰረት ባስተሳሰብም ይሁን የኢትዮጵያን ህዝብ ጭቆና በመረዳት እና መፍትሄ ማግኘት ብዙም ልዮነት ያልነበራቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የገጠመው ግብግብ የተለየው በኃላም የተቋጨውም በያዙት የጦር መሳርያ መጠን እና በነበራቸው የመንግስትነት ቀረቤታ ነው፡፡ ለዚህም ነው በኢህአፓ ውስጥ የነበሩ አንጃዎች ራሳቸው በፍጥነት በመቀየር ጉራ ለይተው ወደ ወታደራዊው መንግስት መለጠፍ እና በመጨረሻ ወደ እሳትራትነት እንዲቀየሩ ምክንያት የሆነው፡፡

በአንፃሩ የቆሙት እንደ እነ ኢህአፓ እና ኦነግ አይነቶቹም በከፍተኛ ደረጃ የቀይሽብር ሰለባዎች ሆነው ነፃ እናወጣሃለን የሚሉትን ህዝብ ነፃ ማውጣት ይቅርና ራሳቸውንም ማቆየት በማይችሉበት ደረጃ ላይ የወደቁት፡፡

1967-1968 ዓ/ምበነበሩት ሁለት አመታት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከስነሐሳብ ፍጭት እና የአርዮት ዓለም ግጭቶት እና ሙግቶች በዘለለ በተግባር ወደ ትጥቅ ትግል የገቡበት ወቅት ነው፡፡ በነዚህ ዓመታት ተሓህት፣ ተሓህት ጠራናፊት (በኋላኢድዮ)፣ኢህአፓ (ኢህአሰ)፣ ግገሓት እና የመሰሳሰሉት ሲሆኑ በተለይ ከላይ የጠቀስኳቸው የፖለቲካ ድርጅቶች የትጥቅ ትግል የጀመሩት በአሁኑ የትግራይ ክልላዊ መንግስት በወቅቱ የትግራይ ክፍለሃገር/ጠቅላይ ገዛት ነበር፡፡

የትግራይ ህዝብ በታሪክ ኢትዮጵያ ከመሰረቱ ህዝህቦች በቀዳሚነት የሚቀመጥ እና በአንድም ወቅት ኢትዮጵያ ከምትባለው አገር ለቀናትም ወጥቶ ወይም በሌላ አስተዳደር ስር ሆኖ የማያውቅ ህዝብ ነው፡፡ በዘመነ መሳፍንት ወቅት እንኳን ብናይ ኢትዮጵያ የሚባለውን አገር ይዘውት የነበሩ እና የቆዮ አካባቢዎች ደጋው የአሁኑ ኤርትራ አካባቢ መላው ትግራይ እንዲሁም የተወሰነ የጎንደር አካባቢዎች ብቻ ነበሩ፡፡

የትግራይን ህዝብ ኢትዮጲያዊነት መጠራጠር "በማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ!"እንደሚባለው የአበው ብሂል ነው፡፡ የትግራይ ህዝብን ማንነት "ታሪኽ ኢትዮጵያ" በሚል በደብተራ ፍስሃጊዮርጊስ ዓብየዝጊ የተፃፈው መፅሀፍ ላይ "ንሕና ጦብያ ደአንበሃል እምበር ሓበሻ አይንባሃልን"ትርጉሙም እኛ ኢትዮጵያዊያን እንጂ አበሻ አንብልም ሲሉ ኢትዮጵያዊነት እና የትግራይ ህዝብ የአንድ ሳንቲም አንድ ገፅታ እንደሆኑ ከዓድዋ ጦርነት በፊት ተፅፎ በፈረንጆቹ 1897ዓ/ም የታተመው መፅሃፋቸው ፅፈዋል፡፡

ለዚህም ነው የትግራይ ህዝብ ለማንኛውም የኢትዮጵያ ስም ለያዘና የኢትዮጲያ ህዝቦችን ከባርነት ነፃ ለማውጣት አታገላለሁ ለሚል ድርጅት በስሙ ከተደራጁ ድርጅቶች አኩል ሲንከባከብናአብሯቸው ሲታገል ከነበሩ ድርጅቶች ለአብነትም እንደነ ኢህአፓ/ኢህአስ ኢዲዮ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይችላላ፡፡

## የህውሓት ምስረታ እና ሂደት

ህውሓት/ተሓህት በ1967 ዓ.ም ወርሃ የካቲት ወደ ትግራይ በረሃ ደደቢት ሲወጣ በጣት የሚቆጠሩ አባላት ነገር ግን በትልቁ ያለሙ እና በፅናት ለመታገል የወሰኑ ወጣቶች ነበሩ፡፡ ተሓህት በ1967-1970 ዓ.ም ከሞላ ጎደል በተማሪዎች እና ጥቂት የመንግስት ሰራተኞች የተወጣጡ ከመሆናቸው በዘለለ ይህ ነው የሚባል አስተዳደራዊም ይሁን የፖለቲካ አደረጃጀት ልምድ የሌላቸው ወጣቶች ሰለነበሩ መደራጀት እና ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር ከፈተናዎች አንዱ ነበር፡፡

ማንኛወም የፖለቲካ ድርጅት በመጀመሪ የመደራጀት እድሜው ከሚያጋጥሙትና መታለፍ ከሚገባቸው ፈተናዎች አንዱ ድርጅታዊ ልሂቅ (organizational elite) መፍጠር መቻልና አለመቻል ነው፡፡ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ድርጅታዊ ልሂቅ መፍጠር ሲችል፤ ይህ የተፈጠረው ልሂቅ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንቦችን፣ የአባልነት መመልመያ ስርዓትን ያወጣል ይቆጣጠራል፡፡ ይህ ማለት በድረጅቱ የሚገቡትን እና የሚወጡትን ሰዎች (አባላት) የመቆጣጠርና የቀን ተቀን ዉሎዋቸውን የመወሰን ሙሉ አቅምና ስልጣን ያለው አካል ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

ይህን የድርጅቱን አባላት የመቆጣጠር አቅም ያገኘው ልሂቅ የድርጅቱን የፖለቲካ አቅጣጫ የመወሰን ሙሉ ስልጣን ይይዛል: በዚህም መሰረት የድርጅቱ የፖለቲካ መስምር (organizational ideology) በዚህልሂቅ ይሁንታ ላይ የተመሰረተ ይሆና ማለት ነው፡፡

ተሓህት/ህውሓት በ1969 ዓ.ም አጋጥሞት የነበረው ግርግር (ሕንፍሽፍሽ) መሰረታዊ ምክንያት ሊመነጭ የሚችለው ከላይ ከገለፅኩት የአንድ ድርጅት የፖለቲካ ልሂቅ የመፍጠር ሂደት(Genesise) መሰረት ነው፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት የልሂቅ ፈጠራ ሂደትን የግድ የሚያደርጉ መሰረታዊ ጉዳዮችን ብንመለከት፡፡

1. በማንኛውም ድርጅት ቀድመው ሊሰባሰቡ የሚችሉት በተመሳሳ የኢኮኖሚ ፣ ተቀራራቢ የማህራዊ መሰረት የሚገኙና አንድን የፖለቲካ አመለካከት በተቀራራቢ እይታ የሚያዮ ሰዎች ናቸው፡፡

2. ማንኛውም ድርጅት በአነስተኛ ቁጥር ስለሚጀመር በጀማሪው አባል እና በጀማሪው አመራር መካከል የሚኖረው ቅርርብ እጅግ የጠበቀ ነው፡፡የሚፈፀሙት ስህተቶች በቀላሉ ለአባላት የሚታዮ ከመሆናቸውም በላይ በጠበቀ ዲሲፐሊን የተያዙ ስለማይሆኑ እንዲሁም ከላይ ከገለፅኩት ተቀራራቢ የማህበራዊ መሰረት ጋር ተያይዞ እያንዳንዱ አባል ራሱን በመሪዎቹ ቦታ ለማስቀመጥ እና መወሰን እንደሚችል ያስባል፡፡
3. የመሪነት ውድድሩ መጥበብ እና እንዳንዱ አባል የመሪነት ቦታ የመያዝ እድሉ መስፋት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከላይ በገለፅኳቸው ምክንያቶች በኢትዮጲያ በተለም በ1960ዎቹ ተፈጥረው የነበሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች አመሰራረታቸው ከኢዲህ/ ጠራናፊት በስተቀር ሁሉም በተመሳሳይ የፖለቲካል ኢኮኖሚ መሰረት ላይ በነበሩ የማህበርሰብ ክፍሎች የተመሰረቱ ነበሩ፡፡

ለአብነት

1. **ኢህአፓ/አህአሰ**

የኢህአፓ አመሰራረት ሂደት ውስጥ ሳልገባ ኢህአፓን የመሰረቱ አባላትን ኢኮኖሚያዊና ማበራዊ መሰረት ብንገመግም አገራችን በነበረችበት ሁኔታ የተማሩ፣ በመካከለኛ እና ከፍተኛ ገቢ የሚተዳደር የማህበረሰብ ክፍል የተወጣጡ በመሰረቱም በወቅቱ በህዝቡ በስፋት ይራመድ የነበረው የግራዘመም ፖለቲካ አራማጆች የነበሩ ሰዎች ናቸው

ምንም እንኳን በከፍተኛ ስሜታዊነት እና ግብታዊነት እጅግ ብዙ ወጣቶች ኢህአፓን የተቀላቀሉ ቢሆንም የኢህአፓ ኮር ግን ትልቁን የቤት ስራውን ጨርሶ ሳይሰራ እና ስልጣን በአቋራጭ ወደሚገኝበት አቅጣጫ በማተኮሩ ምክንያት ድርጅታዊ ልሂቅ(party elite) መፍጠር ሳይጀምር ወደ መተራመስ ነው የገባው፡፡ በዚህም ምክንያት ኢህአፓ እንደ ፓለቲካዊ ፓርቲ በጠበቀ ዲስፐሊን የሚመራበት መተዳደርያ ስርዓት ማበጀት ሳይችል ቀጥሎም ድርጅታዊ ስነ ሓሳቡን ሳያጠራ የፖለቲካ አቅጣጫውን (political ideology) ሳያነጥር ወደ አመራር ቦታ የመቋመጥ ትርምስ እንዲገባ ሆኗል፡፡ ኢህአፓም የዚህ ውስጣዊ ትርምስ ሰለባ በመሆኑ መበታተን እጣ ፋንታው ሆኖ አሁን ወደምናውቀው ደረጃ ወርዷል፡፡

አንዳንድ የፖለቲካ ገምጋሚዎች የኢህኢፓ መፍረስ ከገጠመው ውጫዊ ጫና ጋር ያይዙታል በኔ እምነት ውጫዊ ግጭቶች እና ውጫዊ ጫናው እጅግ ዝቅተኛ ተፅእኖ ብቻ ነው መፍጠር የቻለውም የሚችለውም፡፡

2. **መኢሶን፣ኢጨአት፣ማሌሪድና ወዝሊግ**

የጠቀስኳቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ከመኢስን በስተቀር በኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም እንኳን ይህ ነው የሚባል አስተዋፅኦ ባይኖራቸውም ከላይ በገለፅኩት ድርጅታዊ ልሂቅ

በመፍጠር ሂደት ውስጥ የነበረባቸው ድክመት ወይምን የፖለቲካ ውሳኔ ከድርጅታዊ ልሂቅ ምስረታ ጋር አያይዤ ለመግለፅ ስለፈለኩ ነው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ፖለቲካዊ ልሂቅ በመፍጠር በኩል ከፍተኛ ከክፍተት ስለነበረባቸው ራሳቸውን ወደ ተፈጠረ ወይም ልሂቅ ፈጥሮ ፖለቲካዊ ስነሃሳቡን ወዳስቀመጠ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም አደረጃጀት ራሳቸውን ማስጠጋት ነበር የመረጡት፡፡

በወቅቱ ከነበሩት አማራጭ አደረጃጀት አብዮታዊ ሰደድ (ወታደራዊው ደርግ) የተሻለው ስለነበረ እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀላሉ ወደተፈጠረው የአብዮታዊ ሰደድ ፖለቲካዊ ልሂቅ ራሳቸውን ማስገዛት እና ይህ ቡዱን እንደ መሪ መቀበልናኢማሌድህን በማቋቋም የአብዮታዊ ሰደድ ተለጣፊ ተስፈኛ ሆነው ለትንሽ ጊዜ ከቆዩ በኋላ በራሱ በአብዮታዊ ሰደድ/ኢሰፓ ተበልተው እስኪጠፉ ድረስ መጠለልን መርጠው ነበር የቆዩት፡፡

### 3. አብዮታዊ ሰደድ/ኢሰፓ

አብዮታዊው ደርግ ከወታደራዊ የመኮንኖችና ባለ ሌላ ማእረግ ስብስብነት ጀምሮ እስከ ተጠናከረ ኢስፓ ድረስ ለመድረስ ቀላል የማይባል ሽኩቻና መገዳደል አሳልፏል፡፡

በለውጡ የመጀመርያ እንቅስቃሴ እንደ ወታደራዊ ኮሚቴ ተቋቁም ከነበረው የመኮንኖችና የባለ ሌላ ማዓርግ ስብስብ እስከ መንግስቱ ኃ/ማርያም የአደረጃጀቱ ብቸኛ ልሂቅ ሆኖእስኪወጣ ድረስ ከፍተኛ መጠፋፋት እና ሽኮቻ ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡

የወታደራዊው ደርግ የመምራት እድል እንኳን ቢያገኙም ልሂቅ ሆነው መውጣት እና ተከታይ አፍርተው የመታዳደርያና የዲስፕሊን ስርዓቱን አበጅተው የፖለቲካ ርእዮት አለሙን (political Ideology) መቆጣጠር ደረጃ ላይ ሳይደርሱ በፍተጊያውና በስልጣን ሽኩቻው ተጠልፈው የቀሩት መሪዎችን መጥቀስ ይችላል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ጀኔራል አማን ዓንዶም፣ ጄኔራልተፈሪ በንቲና ኮ/ል አጥናፉ አባተን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በውስጣዊ ሽኩቻ በከፍተኛ ደረጃ ተጠምዶና የፖለቲካ ልሂቅ ለመፍጠር የማያባራ የውስጥ ትግል ያደርግ የነበረው ወታደራዊው ደርግ በተለይ በ1969 ዓ.ም ግልፅያለና የመሪነት ቦታው ያለተቀናቃኝ መያዝ የቻለው የ ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርም ቡዱን የውስጥ ደንብና ስርዓቱን በተጠናከረ መንገድ መፍጠር እና መቆጣጠር ከመቻሉም በላይ ውስጣዊ አደረጃጀቱን በወቅቱ ከነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እንቅስቃሴዎች በተሸለ ደረጃ ራሱን አደራጅቶ የፖለቲካ ርእዮት አለሙን ግልፅ በማድረግ ከውስጣዊ ሽኩቻው በመውጣት ወደ ውጭ ጠላቶቹ የመዝመት ዓቅሙን አግኝቷል፡፡ ከዚህ በመነሳትም "አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል"ብለውበማወጅ የውጭ ጠላቶቻቸው ላይ ዘመቻ የጀመሩት፡፡

ደርግ እንደ ፖለቲካዊ አደረጃጀት ብቻ ሳሆን እንደ መንግስትም የተሟላ መንግስታዊ መዋቅር ፈጥሮ በኮ/ል መንግስቱ ዙረያ የሚሽከረከር ብቸኛ ልሂቅ ሆኖ ውጣ፡፡

ከተጠቂ የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀቶች ውስጥ አንዳንዶቹ የአብዮታዊ ሰደድ/ደርግ ተጠናክሮና ድርጅታዊ ልሂቅ ፈጥሮ መውጣቱን የተገነዘቡ ነገር ግን ራሳቸውን ችለው መቆም ያልቻሉት እንደ መኢሶን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ራሳቸውን በሰደድ ጉያ ዉስጥ ሊዎሽቁ የቻሉት፡፡

## 4. ከኤርትታ ድርጅቶች ውስጥ

የኤርትራድርጅቶች የአመሰራረት ሂደታቸውን ሳልዳስስ ከተናሳሁበት ድርጅታዊ የፖለቲካ ልሂቅ ምስረታ ላይ የነበራቸውን ሂደት ባጭሩ ብዳስስ፡-

### 4.1 ጀበሃ/ELF

ጀብሃን የመሰሩቱ ግለሰቦች በኢትዮ/ኤርትራ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚታይ ሚና(Active role) የነበራቸው ግለሰቦች በግብፅ መንግስት አደራጅነት (አጋዥነት) የተመሰረቱ ናቸው፡፡ በዚህ የምስረታ ጊዜ እንደማንኛውም የሚደራጃ (ተመስራች) የፖለቲካ ፓርቲ በተመሳሳይ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሰረት ላይ የነበሩ ግለሰቦች ናቸው ፡፡ ይህ በግብፅ ካይሮ ተመስርቶ ወደ ኤርትራ በርሃዎች የገባው የፖለቲካ ድርጅት የኤርትራ በርሃ መግባቱ እንደታወቀ ቀድመው በስፋት የተቀላቀሉት በአረብ አገሮች እና ኢትዮጲያ/በኤርትራ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የተማሩ፣ በፖለቲካው ይሳተፉ የነበሩ ወይንም በተለያየ የግል ስራ ላይ የነበሩ ከማህረሰቡ አወቃቀር አንፃር ላቅ ያለ የመደብ ከፍታ የነበራቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ጀብሃ እንደተመሰረተ ከነበሩ ሽኩቻዎች ውሰጥ ድርጅቱን በልሂቅነት የመቆጣጠር ፍትጊያ አንዱ ነበር፡፡ ጀብሃ ከተመሰረተበት በተለይም በረሃ ከገባበት ከ1961እ.ኤ.አ ጀምሮ ያለማቋረጥ ውስጣዊ የስልጣን ሽኩቻ የሚታወቅ ከመሆኑም በላይ በተለይም በስፋት የሚታወቀው የ1970 እ.ኤ.አ በጀብሃ ውስጥ የተፈጠረው ውስጣዊ አደረጃጀቶች እና ጀብሃ ውስጥ ሆነውነገር ግን ራሳቸውን የቻሉ የፖለቲካ ማህበሮች በብዛት ተመስርተው ነበር፡፡

በተለይም በ1971 ዓ.ም የአሁኑ (ሻዕቢያ) የያኔው ህዝባዊ ሓይልታት ራሱን ከጀብሃ ነጥሎ ካወጣ በኋላ በተመሳሳይም መንግድ በኦስማን ሳልሕ ሳበ የሚመራ ሌላ ቡድን ራሱን ከጀብሃ ነጥሎአወጣ፡፡

በጀበሃ ውስጥ የዚህ ዓይነት በድርጅት ደረጃ ሊገለፅ የሚችል ጀብሃን የመቆጣጠርና ልሂቅ ሆኖ የመውጣት ውስጣዊ ሽኩቻ ለየት ባለ መልክግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ ከመሆን ይልቅ ድርጅታዊ መልክ የያዘ ነበር፡፡ ይህ ፍትጊና ሽኩቻ ጀብሃን እንደ ድርጅት እያዳከመ እና ውስጣዊ ጥንካሬ ያለው ድርጅታዊ ልሂቅ ሳይፈጥር በመቅረቱ እና የመፍጠር ሂደቱ ባለማለፉ ምክንያት ከውጭ ከተፈጠረበት ጫና በበለጠ ጀብሃ ማለፍ ያቃተው ይህ ውስጣዊ የድርጅታዊ ልሂቅ ፈጠራ ሂደት ዳገት መውጣት አለመቻሉ ነበር፡፡ በመሆኑም ጀብሃ መፍረስ የጀመረው ከውስጡ ነበር፡፡ ይህ ከውስጥ የመፍረስ ሂደት በውጫዊ ግፊት ወይም ግጭት የጀብሃ መፈረካከስ ሂደት ማፋጠን ላይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡

## 4.2 ህግሓኤ/EPLF

ራሱን ከጀብሃ ለይቶየወጣው ህግሓኤ ከዋናው ድርጅቱ ተነጥሎ ከወጣ በኋላ ምንም ዓይነት መፈናፈኛ ሳይሰጥ ነገር ግን ጠንከር ያለ እርምጃ በመውሰድ የጀመረው የድርጅታዊ ልሂቅ የመፍጠር ሂደት ከሌሎች የአካባቢ ድርጅቶች ለየት ባለ መንገድ ከእያንዳንዱ አባል ወደ ድርጅቱ ሲገባ ጀምሮ በወንፊት እየተበጠረ እንዲገባ የሚያደርግና ልሂቅ የመሆን ህልም ወይም ምኞት ያላቸው ግለሰቦችን በመመዘን (quaranteen) በማድረግ የሚጀምር ነበር፡፡ ይህ የፓርቲ ልሂቅ የመፍጠር ሂደት በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ላይ የተመሰረተ እና የእሳቸውን የፖለቲካ አስተሳሰብ መሰረት ባደረገና እሳቸው ያስመሩትን መስመር በማይተላለፍ መንገድ እየተዋቀረእንዲሄድ ተደርጎ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ አቶ ኢሳያስ ያወጡትን ውስጣዊ ደንብ እሳቸው የሚያስቡትን ሃሳብ በመቃወም ሊመጣ የሚችለውን ሽኮቻ በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲሄድ የሚያደርጉ አሰራሮችን ጠበቅ ባለ መመርያ ተግባራዊ ከማድረጋቸውም በላይ በመስራችነት የስልጣን ተቀናቃኝ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩትን እንደነ አቶ አብርሃም ተወልደ እነ አቶ ሰሎሞን የመሳሰሉትን በማስወገድ ተጀምሮ ህግሓኤ ልሂቁን አንጥሮ እስኪያወጣ ድርስ ተጎዟል፡፡የድርጅቱን የመተዳደርያ ዲስፐሊን እንዲሁም የፖለቲካ ርእይቶ አለሙን በእሳቸው ቁጥጥር ስር እንዲሆን እና ድርጅት ማለት የህግሓኤ ልሂቁ በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂዙርያ እንዲገነባ ተደርጓል፡፡ በዚህም ንሕናን ዕላማናን በሚለው ፅሁፋቸው አሳቸውንና አላማቸውን ያነጠሩብት ስነሃሳብ ይዘው ህግሓኤን ፈጠሩ፡፡ ስለሆነም በኔ እምነት ህግሓኤ ከፈጣሪዋ በኋላ እነደ ድርጅት ለ አነድ ቀን መቆም ትችልም፡፡

## 5. ተሓህት/ህወሓት

የህወሓት አመሰራረት ላይ ብዙም ሳላተኩር ድርጅቱ ከተመሰረተ በዓመት ውስጥ ተመሳሳይ የፖለቲካና ማህበራዊ መሰረት ያላቸው ሰዎች በብዛት ተቀላቀሉት፡፡ በስም ይታወቁ ከነበሩ መስራች አባላት በተጨማሪ ማህበራዊ መሰረቱን ሳይለቅ የአባላቱ በዛት እየጨሩ በመሄድ ምክንያት የድርጅቱን የመሪነት ሚና ማን ይቆጣጠረው የሚል ማንኛውም ተመስራች ድርጅት (infant organization) የሚያጋጥመውን ልሂቅ የመፍጠር ጥያቄ መመለስ ነበረበት፡፡

በተለይ በ1969 ዓ.ም በድርጅቱ ተፈጥሮ በነበረው ድርጅታዊ ቀውስ (ሕንፍሽፍሽ) መሰረታዊ ጥያቄው ድርጅቱን የመምራትና የድርጅታዊ ልሂቅ (organizational elite) ሆኖ የመውጣት ጥያቄ ነው፡፡ በድርጅቱ የታሪክ ትምህርት ላይ የዛን ወቅት ሁኔታ ሲገልፁት የድርጅቱን ስልጣንየዓድዋ አክሱም እና ሽሬ የተወላጆች ተቆጣጥረውታል የሚል የመሻኮቻ ሃሳብ የያዙ አባላት ያነሱት ግርግር እንደነበረ ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ይህን ጥያቄ የሚያነሱት ሰዎችም ሳይቀሩ ከነዚህ አካባቢዎች የመጡ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ትግራይ በሚባው ቦታም ድርጅቱን በወቅቱ ይመሩ ከነበሩት ጋር በአብሮ አደግነትና በዝምድና የተሳሰሩቱ ነበሩ፡፡ ስለዚህ በመሰረቱ በወቅቱ ድርጅቱ አጋጥሞት የነበረ

ውስጣዊ ትግል ልክ እንደ ማኛውም የፖለቲካ ስብሰብ የድርጅቱ የመሪነት (የልሂቅነት) ቦታ የመቆጣጠር ትግል ወይም ሽኩቻ ነበር፡፡

በወቅቱ በእነ አረጋዊ በርሀ(በሪሁ) ይመራ የነበረው ቡድን የሚችለውን አቅሙን በመጠቀም የበላይቱን ሊያረጋግጥ ችሏል፡፡ የበላይነቱን እንዳረጋገጠ በፍጥነት ያደረገውም የድርጅቱ የዲስፕሊን ስርዓት (ውስጠ ደንብ) ማውጣትና የድርጅት ባለቤትነቱን ማረጋገጥ ነበር፡፡

ባለቤትነቱን ያረጋገጠው ቡድን ድርጅታዊ ማጥራት ያለማቋረጥ ለሁለት ዓመታት ካደረገ በኋላ በ1971 ዓ.ም የመጀመርያ ድርጅታዊ ጉባኤውን በማድረግ ህግና ስነስርዓት (የውስጥ ደንቡን) እንዲሁን ርኢይቶ አለም ቀርፆ የፖለቲካ ፓርቲ ልሂቅነቱን (organizational elite)አንጥሮ አወጣ፡፡ ይህ ውስጣዊ ትግል አድርጎ ነጥሮ የወጣው ፖለቲካዊ ልሂቅ ድርጅቱን እና የድርጅቱን ሁለንተናዊ ህልውናና ውስጣዊ ደንብና ስርኣቱን በመቆጣጠር ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ለየት በለ መንገድ የቡዱናዊ ልሂቅነት ህልውናውን አረጋገጦ ወጥቷል፡፡

ይህ በልሂቅነት ጎልቶ የወጣው ቡድን ድርጅታዊ ባህል (organaizional calture) ወደ መፍጠሩ ተሸጋግሮ እጅግ ኋላቀር ከሆነ አካባቢ የተነሳው ህውሓት የትግራን ህዝብ አስተባብሮ የኢትዮጵያ፤ ብሎም የአፍሪካን ከዛም አልፎ በዓለም ደረጃ ሊደመጥ የሚገባው ሃሳብና አመክንዮን ይዞ ብቅ አለ፡፡

በኢትዮጲያ/ኤርትራ ፖለቲካ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ጉሉህ ሚና የነበራቸውና የተሳካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢሰፓ፣ህወሓት እናህግሓኤ ብቻ ነበሩ፡፡ለጉልህነታቸውና ለስኬታቸው እንዲሁም ከፍ ያለ ሚና እንዲጫወቱ ያደረጋቸው ከሌሎች ወይንም በዚህ ደረጃ ሊወጡ ካልቻሉት የፖለቲካ ድርጅቶች በተለየ የፖለቲካ ፓርቲ ምስረታ ሂደታቸውን የጨረሱ መሆናቸው ነው፡፡

እዚህላይ ግልፅ ማድረግ የምፈልገው ማንኛው ድርጅት ይወለዳል፣ያድጋል፣ይበስላል፣ያረጃል/ይታደሳል ሊሞትም ይችላል፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ግን ማደግ ደረጃ ላይ ሳይደርሱ ተወልደው የፖለቲካ ልሂቅ እና ድርጅታዊ ርእይቶ አለም ሳይፈጥሩ ለረጅም ጊዜ እየተንከባለሉ ራሳቸው ለፖለቲካ መሪነት ሳይዘጋጁ በስመ ድርጅትነት ሊቀመጡና ስሜት እና ስሜት ኮርኳሪዎች ብቻ ሆነው ለረጅም አመታት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለአብነት በአገራችን ሁኔታ ኢህአፓ፣ኦነግ፣ኦብነግ እና የተለያዮ የኤርትራ ፖለቲካዊ ቡድኖችና መውሰድ ይችላል፡፡ እንደኔ እምነት የበሰለድረጅት የፖለቲካ ስልጣን የመያዝና መንግስት የመሆን አደረጃጀት በሂደት ይፈጥርና ራሱን እጩ መንግስት በማድረግ እንዴት ከተቀናቃኝ ድርጅቶች አንድሚለይ አነጥሮ ያሳያል፡፡

## <u>ህውሓት በኔ እይታ</u>

ህውሓትን ከወሬ ከስማበለው በዘለለ በአካል ያወቅኩት 1976 ዓ.ም እንዳጋጣሚ ሆኖም ግንቦት 20 1976 ዓ.ም ነበር፡፡ ህውሓት ውስጥ ከወላጅ አባቴ ጀምሮ አጎቴ የአጎቴ ልጆች እንዲሁም የአያቴ

ታናሽ እህት ልጆችና የልጅ ልጆች በብዛት የታገሉበት ድርጅት ነው፡፡ ህውሓትን ከፖለቲካዊ እውቅና በተጨማሪ የቤተሰብ ተሳትፎው በርካታየነበር ቢሆንም የኔ እይታ እንዲመዘንልኝ የምፈልገው ድርጅቱን በምገመግምበት ፖለቲካዊ ነጥቦች ብቻ እንዲሆንልኝ እፈልጋለሁ፡፡

በ1976 ዓ.ም ህውሓትን ስቀላቀል ቤተሰባዊ እውቅና እንጂ ፖለቲካዊ እውቀት ኖሮኝ አልነበረም ምክንቱም በወቅቱ እድሜየ ገና 14 ዓመት ከመሆኑም በላይ ለምንም የድርጅቱ የፖለቲካ ፅሁፍም ይሁን የድርጅቱ አባል የመገናኘትና የማግኘት እድል ገጥሞኝ አያውቅም፡፡ ግንቦት 20 1976 ዓ.ም ዓዲ አርባዕተልዩ ቦታው ሓርሽ በሚባልአካባቢ በኩል ከህወሓት አባላት ጋር ተገናኘሁ አንድ ሳምንት ከቆየሁ በኋላወደ ጭላ ተወስጀ ከድርጅቱ የአካባቢው ክፍለ ህዝብ ጋር የመተዋወቅ እና በወቅቱ ስለ ወላጅ አባቴ የሚኖርበት አካባቢ ከማወቅም በላይ አጠር ያለ የፖለቲካ ትምህርት ለማግኘት እንዲሁም የመታገል ስሜት እንደፈጠረብኝ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በወቅቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪ የነበርኩ ሲሆን የተወሰነ የፖለቲካ ትምህርት ያስተማረኝ አረፋይኔ የተባለ ታጋይ ይገለፅልኝ የነበረን የትግራይ ህዝብ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚዊ ሁኔታ ለመረዳት ብዙም አልተቸገርኩም፡፡

ጭላ አካባቢ በቆየሁበት የ10ቀን ቆይታየ አባቴን የማግኘት ውሳኔን በማዘግየት ወደ ማሰልጠኛ የመግባት ፍላጎቴን በመግለፅ በ1976 ሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ተከዜ ወደሚገኘው የማሰልጠኛ ጣብያ ተቀላቀልኩ፡፡

የማሰልጠኛ ጣብያ ስደርስ የተቀበለኝ ሰው አሁን ከሃገር መከላከያ ሚ/ር በጥሮታ የወጣ ኮ/ል ተጫኔ አባይ የሚባል ነበር፡፡ በወቅቱ የማሰልጠኛ ጣቢያው የፐርሰኔል ኃላፊ የነበረው ይህ ሰው ወደምሰለጥንበት ሻለቃ መደበኝ፡፡

ተከዜ የተሰጠን ስልጠና ጨርሰን ጥቅምት 1977 ዓ.ም ወደ ማእከላይ ወታደራዊ ጽ/ቤት የቶፓግራፊ ክፍል (አዲስ ክፍል ነበር) እኔና ታደሰ መረሳ ከተባለ ታጋይ ጋር ተመደብንይህ ክፍል የነበረበት ቦታ ከምዕራብ ትግራይ (ተከዜ) የራቀ ቦታ ስለነበረ ረዘም ላለ ማለተም ለአንድ ሳምነት ሙሉ መጓዝ ነበረብን፡፡ ከሳምንት ጉዞ በኋላም ማእከላይ ትግራይ ተንቤን ውስጥ ጫሞ የተባለ የህውሓት የድርጅት ማእከል ደርሰን ከላይ ወደ ገለፅኩት ክፍል ተቀላቀለን፡፡

በዚህ ጫሞ በተባለ ቦታ የህውሓት ማእከላይ ኮሚቴ ፅ/ቤት፣ የወታደራዊ ፅ/ቤት፣ የፖለቲካ ፅ/ቤት የህዝብ አደረጃጀት ፅ/ቤት እንዲሁም የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፅ/ቤት የነበሩ ሲሆን በወቅቱ አባቴም እዚህ ቦታ ስለነበረ ለማግኘት እድሉን አገኘሁና፡፡ በህፃንነት የማውቀውን አባቴን በ15 ዓመቴ አገኘሁት፡፡ በዚህ ወቅት የድርጅቱ መሪ አቶ ስብሓት ነጋ፣ የህውሓት ወታደራዊ ፅ/ቤት ኃለፊና ኮማንደርን አቶ አረጋዊ በርሀ ምክትላቸውንአቶ ስየ አብርሃን፣ አቶ መለስ ዜናዊን፣ አቶ ግደይ ዘርአፅዮነን፣ አቶ አውዓሎም ወልዱን እና ሌሎች የፖሊት ቢሮ እና የመ/ኮሚቴ አባላትን ተዋወቀኩ፡፡ በተለይ በፍጥነት ወደ ድርጅቱ የአኗኗር ባህል ለመግባ ያስቻሉኝ ብዙ ወጣት ታጋዮችን መተዋወቄ ነበር፡፡

በተመደብኩበት በወታደራዊ ፅ/ቤት የወታደራዊ ቶፖግራፊ ክፍል ውስጥ የነበሩ አባላት ቁጥር ከአምስት የማይበልጡ የነበሩ ሲሆን ከእኔ ጋር አብሮኝ የተመደበው ታደሰ መረሳ ተስፋሁነኝ ጋር የአጭር ጊዜ (የአንድ ሳምንት) ስልጠና ተሰጥቶን ወደ ስራ ተሰማራን፡፡

በ1977 ዓ.ም ህውሓት በከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ የነበረ ሲሆን በወቅቱ የነበረው አመራር በርግጥም የትግራይን ህዝብ መርቶ/ታግሎ እና አታግሎ/ ወደ ተፈለገው ድል ሊያደርስው የሚችል መሆን እና አለመሆኑ የሚፈተንበት ወቅት ነበር፡፡

በትልቁ በሃገር ደረጃ የሚታወቀው የ1977 ዓ.ም ድርቅ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ህዝብ ያለቀበት አገር ጥሎ የተሰደደበት እና ይህ ህዝብ ከጥፋት ማዳንና ያለማዳንየህልውና የሚረጋገጥበት ወቅት ነበር በሌላ በኩል ደርግ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ህውሓት ይገኝበታል ብሎ የሚያስበውን ቦታ በሙሉ ያሰሰ ከመሆኑም በላይ የትግራይን ህዝብ ከትግሉ ለማራቅ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡ በሌላ በኩልም ህወሓት በውስጡ ይፈጠሩ የነበሩትን ፖለቲካዊ ልዮነቶችን የማጥበብ ወይም የመፍታት ውጥረት ውሰጥ ገብቶ የነበረበት ወቅት ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ አንድ ድርጅት መለካት ያለበት ህልውናውን አረጋግጦ ህዝቡን ከዚህ መሰል አስከፊ የድርቅ አደጋ ጠብቆ ውስጣዊ ፖለቲካዊ ችግሩን ፈቶ እና ተጠናክሮ ለመውጣት የሚፈተንበት ወቅት ነበር፡፡

የወቅቱ ህወሓት በውስጡ የበሰለ አካባቢዊ፣ አገራዊ እና አለማዊ ዳሰሳዎችን እና ግምገማዎችን በማድረግ ህዝብና ድርጅት እንዴት እንደሚጠቀም እያሰበ የሚገመግም አመራር እየፈጠረ ስለነበር ከነህፀፁ ወደተሻለ መፍትሄ የሚያመራ እና ቅንነት የተሞላበት አስተሳሰብ የያዘ አመራር ነበረው፡፡ ይህ አመራር ከላይ በገለፅኩት አስተሳሰብ ድርጅቱን እንዲመራ እድል የሰጠው ረዘም ላሉ ጊዜት የህውሓትን ድርጅታዊ ልሂቅነት ያለጥርጥር በሁለት ተከታታይ ድርጅታዊ ጉባኤዎች ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የሚፈልገውን (ለድል ያበቃኛል የሚለውን)ፖለቲካዊ ርእዮቶ አለም የመቅረፅ ባለ ሙሉ መብታና ስልጣን መሆኑን ያረጋገጠ አመራር ስለነበረ የመውረድም ይሁን ከቦታው የመነሳት አደጋ ያልተጋረጠበት የድርጅታዊ ልሂቅ ስብስብ ነበር፡፡

እዚህ ላይ በተለይ ከጠቀስኳቸው ሶስት የፖለቲካ ድርጅቶች የድርጅታዊ ልሂቁ ባህርይየተለየ ነው፡፤ ለምሳሌ በህግሐኤ የድርጅታዊ ልሂቁ ባለቤት አንኳርም አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ሲሆኑ በኢሰፓ በተመሳሳይ መንገድ ከ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ነበሩ፡፡ ለዚህም ነው ኮኔሬል መንግስቱ ኃ/ማርያም አገር ጥለው ሲወጡ መንግስታቸው ከሳምንት በላይ ራሱን ተሸክሞ መኖር ያቃተው እና እንደ ተቋም እንኳን ትንሽ ሊፍጨረጨር ያልቻለው፡፡

በአንፃሩ በህውሓት ውስት የነበረው ልሂቅ በግለሰብ ደረጃ የሚታይ ሳይሆን በቡድን የሚገለፅ ነበር፡፡ ይህ ቡድን የድርጅቱ የአስተሳሰብ ምንጭ ሆኖ በውስጡ ከሌሎቸት ሁለት ድርጅቶች ማለትም ህግሓኤ እና ኢሰፓ በተሸለ ውስጣዊ ዲሞክራሲ የነበረው እና ያለ ይሉኝታ በፓለቲካዊ ጉዳዮቹ የሚከራከር ነበር፡፡ አዲስ ወደ ድርጅቱ አመራርነት የሚየድጉትን አባላት ይመለምላል፣ ይመዝናል፣

እድል ይሰጣል ወይ የነፍጋል፡፡አንዳንድ የማእከላይ ኮሚቴ አባላት ወደ አመራርነት መጥተው ብዙም ሳይቆይ በአንደ ዘመን (4 ዓመት) ውስጥ ከደረጃቸው ይወርዳሉ አዲስ ሃሳብ ይዘው ለመምጣትና የድርጅን ፖለቲካዊ ባህል የሚቀይር አስተሳሰብ ለማንፀባረቅ የዚሁ የድርጅታዊ ልሂቅ ይሁንታ የግድ ነበር፡፡ ይህ ድርጅታዊ ልሂቅ ግን የፈለገውን ዓይነት ፖለቲዊ አስተሳሰብ ተወያይቶ የመያዝ እና ድርጅቱን ከግራዘመምነት(communist ideology) እስከ ነጭ ካፒታሊስት የፖለቲካ እሳቤ፣ ከአንድ ፖርቲ ወይም ሞት እስከ የበዙ ፖርቲ ስርዓት ስብከት ድረስ የመያዝ መብቱ የተረጋገጠ ነበር፡፡ በሌላኛው ጫፍ ህውሓት እንደ ድርጅት የሰከረ ኮሚኒስት በነበረበት ወቅት በኢትዮጵያ/ትግራይ ኮሚኒዝም አይቻልም ካፒታሊዝም ነው የሚቻለው ያሉ አባላት ውጉዝ ከመ አርዮስ ተብለዋል፡፡ አንዳንዱቹም ለእስራት እና ከድርጅቱ እስከመባረር ደርሰዋል፡፡

በአንድ ወቅት የትግል ጥሪ በሚባለው በህውሓት ይታተም በነበረው መፅሄት "ዴሞክራሲ ምንድነው?" በሚል አጀንዳ ዙሪያ ኢህአፓ እና ህወሓት ሲከራከሩ ነበር፡፡ ህውሓትኢህአፓን "ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ" ብሎ ሲሳለቅባት ኢህአፓ ደግሞ "ህወሓት ከድጡ ወደ ማጡ" ብለው ህውሓትን ይተርቡ ነበር፡፡

ከዚህ የሁለቱ ክርክር ውስጥ ኢህአፓ ዴሞክራሲን በሚታወቀውናተለምዷዊ የአቴናዎችን ትርጓሜው በመያዝ መለትም ዴሞክራሲ ማለት የህዝህ አስተዳደር ነው ብሎ ሲከራከሩ ህውሓት ግን ዴሞክራሲ ማለት ስልጣን ማለት ነው በሚል ጠቅለል ባለ እሳቢ ይከራከሩ ነበር፡፡ የበለጠ ሲያብራሩትም ስልጣኑን የያዘው ግለሰብ ከሆነ ዴሞክራሲው የግለሰቡ ነው ሌላው ማህረሰብ ወይህ ስልጣኑን የማይቆጣጠረው የህብረተሰብ ክፍል የዴሞክራሲው ባለቤት ሊሆን አይችልም፡፡ ስልጣኑ የተያዘው በቡድን ከሆነ ዲሞክራሲው የቡድኑ ነው ስለዚህም የዴሞክራሲው ባለቤት ቡድኑ ነው ማልት ነው፡፡ ነገር ግን የስልጣኑ ባለቤት ህዝብ ከሆነ ግን ዲሞክሲው የህዝቡ ነው የሚል ነበር፡፡

በዚህ የህውሓት የዲሞክራሲ ክርክር ውስጥ ማየት የቻልኩት ነገር ቢኖር የስልጣን ባለቤት ማን ነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ የዴሞክራሲው ባለቤት ማን እንደሆነ የመመለስ ያክል አስፈላጊ ነው፡፡ በህውሓት አመራር ድርጅዊ ልሂቅ ውስጥ የተሻለ ዴሞክራሲ የነበረና በልሂቅ ቡድኑ ውስጥ እንደፈለገ የሚከራከረው አካል ወደ አባላቱ በሚወርድበት ወቅት ግን እጅግ የጠበበ ዲሞክረሲያዊ ምህዳር ነበር ይዞት የመጣዉን አጀንዳ አሳምኖ ለመሄድ አንጂ ሃሳብ አንኳን ለመቀበል አልነበረም፡፡ ለአብነት በእያዳንዱ የግምገማ መድክ የመሰለህን አነድትናገር በቅደሚያ ያበርታታና ነገር ግን የመናገር መብትን የሚገድቡ፣አመራሩን ማማት ወይ መውቀስ እንደ ጥፋት የሚገመግሙ ባጠቃላይ አመራሩ ያለውን መቃወም የማይቻልበት ስትቃወም በመቃወምህ የምትገለልበት ፖለቲካዊ ምህዳር የፈጠረ ነበር፡፡

ለዚህም ነው የህውሓት ልሂቅ በ1985 ዓ/ም ማእከላዊ ኮሚቴ ብቻውን ነው የስራው ሌሎቻችሁ አልሰራችሁም በማለት ሁሉን ታጋይ ለማሸማቀቅ የዘመተው፡፡

ህውሓት ውስጣዊ (የድርጅታዊ ልሂቅ) የመናገር፣ የማሰብ ያሰበውን የማራመድ ባለ ሙሉ መብት የነበረ ሲሆን ሌላው አባል ግን ልሂቁ ተነጋግሮ ያመጣለትን ነገር ተግባር ላይ ማዋል፣ ሳይላምጥ የመዋጥ መብት/ግዴታ ብቻ ነበር የነበረው፡፡የዚህ አባባል ጥሩ ማሳያ ለረጅም ዓመታት በውስጡ ሲከራከርበት ሲያነሳውና ሲጥለው የነበረን የፖለቲካ ልይነት እስከ 1977 ዓ/ም ይፋ ሳያደርግ ቆይቶ በ1977 ዓ/ም ሁለተኛ ድርጅዊ ኮንፈረንስ ግን ይፋ አደረገው፡፡

በድርጅቱ ውስጥ ለህዝብ ይፋ ሳያደርግ አንዳድ አቋሞችን ቀየረ ከሙሉ ግራ ዘመም ኮሚኒስት አስተሳሰብ (ከማሌሊት ምስረታ አስክ ድምፅ አልባ ሞቷ) ወደ ሙሉ ካፒታሊስት አስተዳደብ ሄጃለሁ በዚህም የነፃ ገበያ ሰባኪ ሆኛለሁ አሁን ለያዝኩት አቋም የሚመጥን ርእዮት አለም ቀምሪያለሁ ብሎ አብዮታዊ ዴሚክራሲን (revolutionary democracy) አስተዋወቀ፡፡

ከመጀመሪያው እንደተነሳሁበት የህውሓት ልሂቅ ርእዮት አለሙ ባለቤት ስለሆነ የፈለገውን የመቀየር መብት ይዟል ሌላው አባል ከመከተል እና በተግብር የተባለውን ከመተግበር ውጭ ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ ማበርከት አይቸልም፡፡

በሰለጠነው አለም ይህ የፖለቲካ ልሂቅ ከአዳጊ አገራት ልሂቅ የሚለየው የፍጥረት ሂደቱን ስለጨረሰ አብዛኛው ጊዜውን የሚያጠፋው በተቋማትግንባታ ላይ ነው፡፡ ይህ ማለት የፈጠረውን ወይም የሚከተለውን ርእዮተ አለም ወደ ፈፃሚ ግለሰቦች ሳይሆን ፈፃሚ ተቋማትያውርደዋል እነዚህ ተቋማት የአስተሳሰቡ ዋና አስፈፃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ ስለቀጣይነቱም ጭምር በጥናትና ምርምር እያስደገፉ ከትውልድ ትውልድ ያስተላልፉታል ስለሆነም መሰረት ወደረገጠ ስርዓትነት ያሳድጉታል ማለት ነው፡፡ እነዚህ መሬት ረግጠው የተመሰረቱ ተቋማት የማህበረሰብ ፖለቲካዊ ባህል(social and political culture) መገንባት ላይ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያጠፋሉ፡፡ አሁን አደጉ የምንላቸው አገሮች የገነቡት መለያ ባህል አላቸው፡፡ ለምሳሌ ጀርመን ስንል የጀርመኖች መገለጫ የሆነውን የስራ ርቀት ጭንቅላታችን ውስጥ ይመጣል እንግሊዝ ስንል እንግሊዞችን የዳበረ የመናገር ነፃነት ቶሎ ይታየናል እያልን አገሮች የገነቡትን ስርዓትበማህበራዊ ባህል አስደገፈው የህብረተሰቡ ንብረት ያደርጉታል፡፡ ህብረተሰቡም ከሰዎቹ በበለጠ ስርዓቱን በባለቤትነት ይጠብቀዋል ይህ ደግሞ ስልጡን ማህበረሰብ፣ ማህበረሰቡን በተሸለ ደረጃ የሚያገለግል የበለፀገ ስርዓት ይሆንና የፖለቲካ ሊሂቃኑ ቢኖሩም አገርና ህዝብ ተቆራኝተው ለረጅም ጊዜ በሰላም ይኖራሉ፡፡

እንደኛ ዓይነት ባልበለፀገ አስተሳሰብ ውስጥ የሚፈጠሩየልሂቃን ግንመንግስታዊ ስርዓት ምስረታ ግንባታን ከተቋማት ግንባታ ነጥለው ስርዓት ማለት የግለሰቦች ስብስብ የታማኞች ጥርቅም ያደርጉታል፡፡ በዚህ እሳቤም ነው ባንድ ወቅት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለስ ዜናዊ ስለሚኒስትሮቻቸው ሲጠይቁ ቁልፍ መመዘኛ “ለኢህአዲግ ያለው ታማኝነት ነው”ያሉት፡፡

በእውነታው ላይ ብዙም ባልቃወማቸውም በሳይንሱ ግን በጣም ስህተት ነው ባይ ነኝ ወደ በኋላ በስፋት እንደምገባበት ታሳቢ አድርጌ፣ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለስ ዜናዊህወሓት/ኢህአዴግን ከተቋምነት አውጥተው የግለሰብ ንብረት ካስመሰሉት በኋላ ያሉት አባባል

ስለሆነ፣ ለኢህአዴግ ታማኝነት ሲሉ በቀጥታ አባባል ለእሳቸው የታመነ ሚኒስቴር ይሆናል ማለት ነው፡፡

ኢህአዲግ እንደተቋም በተልፈሰፈሰበት ወቅት መላእ ድርጅቱ በእሳቸው ራእይ በሚመራበት ወቅት ድርጀታዊራኢ እንደሌለው ድርጅቱ ዘግይቶም ቢሆን ቢያምን በወቅቱግን አገሪቱም ኢህአዴግም በመለስ ራኢ ይመሩ ስለነበረ ታማኝነት ሲባል ታማኝነት ለመለስ ራእይ ማለት ነበር፡፡

በዚህ እሳቤ ኢህአዴግ ራሱ ተቋም ስላልነበረ ተቋማዊ ራኢ ሊኖረው አይችልም ስለሆነም ተቋማዊ ግንባታ ላይ ጊዜውን አላጠፋም፡፡ ታማኝ ተቋማት ሳይሆኑ ታማኝ ግለሰቦች ነበሩ ኢህአዴግን ያቆሙት፡፡

ለማጠቃለል የድርጅት ልሂቅ የመፍጠር ሂደት እጅግ እልህ አስጨራሽ እና ከተፈጠረም እንደ የቁማር ሳንቲም ወይ ወደ ንጉስ ወይ ወደ ጎፈር የመውደቅ እድሉ ሰፊ ነው፡፡ በአፍሪካ ሁኔታ ስናየው በግለሰብ ልሂቅነት ላይ የተመሰረተ ስረዓተ መንግስታት ስለሚፈጠሩ ከጥቂት አገሮች በስተቀር ተቋም ፈጥረው የመጓዝ አቅም የላቸውም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሚፈጠረው መንግስት በፈጣሪው ልሂቅ እድሜ ላይ ብቻ የሚሽከረከር ይሆንና ከባለፈው ጥሎት ከመጣው ስርዓት ያልተለየ ስርዓት ሆኖበተራው ወዳቂ ስርዓት ይሆናል፡፡ ቅኝ ገዥዎች ባጠገቡ በለፉና በነካኩት ቁጥር በቀላሉ ይወዛወዛል ብሎም ይወድቃል፡፡

ከ1960ዎች ጀምሮ በኢትዮጲያየፖለቲካ የልሂቅ ፈጠራ ሂደት ስናይ ደርግ/ኢሰፖ በግለሰብ ደረጃም በድርጀት የተለጠፉ ከኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ውጭ ያሉ አካላት ኢሰፓን ለመሸከም ያሚያስችል ጉልበት ያልነበራቸው በራሳቸው አንድን የፖለቲካ ፓርቲ መርተው መቆም የማይችሉ ስለ ነበሩ ከኮለኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም አገር ጥሎ መጥፋት ጋር አብረው ጠፍተዋል፡፡

ህውሓት/ኢህአዴግ በበረሃ እየገነባው የመጣውን የቡድን ልሂቅ ተሸክሞ መሄድ የቻለው እስከ 1993 ዓ/ም ብቻ ነበር፡፡ ከ1993 ዓ/ም በኋላ ግን ገንብቶት የነበረውን ቡድናዊ ልሂቅ አፍርሶ በአንድ ግለሰብ (ጭንቅላት) በሚመራ ልሂቅነት ተቀየረ፡፡ በመሆኑም ልሂቁ በሞቱ ጊዜ ሁሉም በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች "የመለሰን ራኢ እናሳካለን ከመለስ ሞት በኋላ ምንም ችግር የለም መተግበር ብቻ ነው እንጂ የ40 ዓመት እቅድ ሰርቶልን አልፏል፤ መለስ ዜናዊ ቢሞትም ጠንካራ መሰረት ያለው መንግስት ትቶልናል ወዘተ" በማለት የገለፁት ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ስልጣን እንደያዙ ስራቸውን የጀመሩት በሽንፈት ነው ያውም እኔ የጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊን ጫማ መሙላት አልችልም በማለት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ከመሞታቸው በፊት የፈጠሩት ክፍተትና የሰሩት ስህተት ቀጥሎ ለሚመጣው ማንኛውም ጠቅላይ ሚኒስቴር እጅግ አዳጋችና የሳቸውን ቀመር ከማጥናት ይጀምርና ባይገባውም እስኪገባው ድረስ ራሱን እንዲቀጣ በማድረግ ስራ ሳይጀምር እየተደነባበረ እንዲቀጥልየሚያደርግ ነበር፡፡

ለምሳሌ በስፋት እንደሚባለው የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር የአገሪቱን GTP1 እና GTP 2 ሰርተው እንዳለፉ በስፋት ይነገራል ፤ነገር ግን ትግበራው ላይ እሳቸው ያረፉት የመጀመሪያው አጋማሽ ላይ ነበር ልክ እንደማንኛውም እቅድ GTP 2 በ GTP 1 አፈፃፀም ላይ መመስረቱ የማይቀር ነውስለሆነም GTP 1 ላይ የሚኖረው ማንኛውም ክፍተት በ GTP 2 ላይ ጫና መፍጠሩ አይቀርም በ GTP 1 ሊያጋጥም ይችላል ተብሎ የተተነበየ ችግር በርግጥ ማጋጠሙና አለማጋጠሙ ካጋጠመስ በምንያክል ደረጃ፣ የተኞችን ዘርፎች ነው በጣም የጎዳው ፤ በሚቀጥለው እቅድስ የትኞችን ነው በጣም ሊጎዳ የሚችለው ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች ነብይ ካልተሆነ በስተቀር አስቀድሞማወቅ እጅግ አዳጋች ነው፡፡ የነዚህ ሁለት አቅዶች 100% ፈጣሪ ሲሞቱ በተቋም ወይም በቡድን ያልተስራ እቅድበመሆኑ ምክንያት ልክ እንደፈጠረው ቀጥለው ለተረከቡት ጠቅላይ ሚኒስቴርም ይሁን ካቢኒያቸው ማደናበሩ የማይቀር ነበር፡፡

ለምሳሌ በGTP 1

አገሪቱ በስኳር ራሷን ለመቻል አቀደች............አፈፃፀሙ 0 ከመቶ

ከ5000 ኪ/ሜ በላይ የባቡር መስመር ታቀደ......አፈፃፀሙ 20 ከመቶ

18000 ኪ/ሜ መንገድ ለመስት ታቀደ..................አፈፃፀሙ 50 ከመቶ

የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት.....................አፈፃፀሙ 0 ከመቶ

እያልን ብንቀጥል በመጀመርያው እና በሁለተኛው እቅድ መካከል የተቀናጀ ቅብብሎሽ ማድረግ የሚቻልበት እድል እጅግ የተበላሸ እንዲሆን አድርጎታል፡፡የዚህ መሰረታዊ ችግር መንስኤም እነዚህ ሁለት እቅዶች የታቀዱትም ሊፈፀሙ የተዘጋጁትም በተቋም ደረጃ ሳይሆን በአንድ ሰው ጭንቅላት በመሆኑ እና ይህንን ያዘጋጀው ሰው በሂወት ሲለይ የአገሬ ሰው እነደሚለው ቁሱም ዝም መፅኃፉም ዝም በመሆኑ ምክንያት ኢህአዴግ/ መንግስት GTP 1 እና GTP 2 መግባባት አልቻሉም፡፡

እየተንሸራተተ የመጣው የህውሓት አመራርበቡድን መመራት አቁሞ በአቶ መለስ ዜናዊ ዙርያ መሽከርከር ጀምረና ከእሳቸው በፊት ከነበሩ የህውሓት መሪዎች ለየት ባለ መልኩ የፈጠራውን ሂደት ወደኋላ በመመለስ ከነበረው ቡድናዊ ልሂቅነት አውጥተው በብቸኝነት የሚቆጣጠሩትና በእሳቸው እስትንፋስ ብቻ እንዲኖር የሚያድረግ የማፈራረስን ስራ ተሳካላቸው፡፡ ህውሓት የሚታዮ ደረጃዎች ያነበሩት ተተካኪና በፖለቲካ አመራር ሰጪ ልሂቃን የተደራጀ መሆኑ ቀርቶ የአንድ የባለ ‘ምጡቅ አይምሮ’ ብቸኛ ንብረት አስኪመስል ድረስ የአቶ መለስ ዜናዊ ብቻ ሆነ፡፡

በ1982 ዓ/ም አቶ መለስ ዜናዊ ከአቶ ስብሓት ነጋ የተቀበሉት የህውሓት አመራር በመሪነትደረጃዎች የተከፋፈለና በውስጡም ለሁሉም ነገር ትግል የሚያደርግየራሱ ውስታዊ ዲሞክራሲዊ (ቡድናዊ ዲሞክራሲዊ) ባህል የነበረው በሃገር ጉዳይ ላይ ተወያይቶ የሚራመድ ነገር ግን ቡድናዊ ስልጣኑን ለማስከበር (ለማስጠበቅ) ሲል ፀረ ዲሞክራሲያዊ አካሄዶች በበታች አባቱ ላይ የሚፈፅም፣ ድርጅታዊ

ህልውናውን በማንኛውም መንገድ የሚያስፈፅም ቡድን ነበር፡፡ በህልሙ ያየውን ነገር ለመተግበር ከመሮጥ ይልቅ እርስበርስ እንደ ሃሳብ አደረጃጀት የነበረው ቡድን ነበር፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ ይህን ድርጅታዊ ባህል ጠብቅው መቆየት የቻሉት ለ10 ዓመታት ብቻ ነበር፡፡ በውስጥ ለውስጥ እየሸረሸሩትና የተናጠል ውሳኔዎች እየወሰኑ እያዳከሙት ከሄዱ በኋላ በ1993 ዓ/ም ይህ እየተሸረሸረ የመጣውና በማህሉ ይዞት የቆየውን ድርትጅታዊ ባህል ያፈረሰው ቡድን ራሱን እንደ ቡድናዊ ልሂቅ መጠበቅ አቅቶት በአንጃ እና በዋናው ቡድን ተከፍሎ ተቧቀሰ ፡፡ በዚህም ህውሓት በውስጣዊ ጥንካሬው ላይ ጦርነት አውጀ ራሱን አቆሰለ፣ አቁሳይም ቁስለኛም ህውሓትን ይመራ የነበረው ራሱ ልሂቁ ቡድን ሆኖ ታሪኩን በማደፍረስ ደመደመ፡፡ ህውሓት በመግቢያየ ላይ እንደገለፅኳቸው የህግሓኤ እና የኢሰፓ ድትጅታዊ ልሂቅ (Organizatonal eliet) ደረጃ ወረደና "በታላቁ መሪ"ጭንቅላተ ውስጥ ብቻ የሚሰራ የአገሪቱን ሃብትና ተቋማት በብቸኝነት የሚቆጣጠር ሲፈልግ 15 ሲፈልግ 20 ሚኒስቴር መ/ቤቶችን የሚበታትንና የሚያደራጅ ፣ በተቋም ደረጃና በቡድን ፖሊሲ ማውጣትን የሚያስብና የሚያወጣ ሳይሆን በአንድ "ምጡቅ" ጭንቀላት ውስጥ ብቻ በሚሽከረከሩ አስተሳሰቦች እርስ በርስ የሚጋጩ፣ አድሏዊነት የበዛባቸው፣ ለልሂቁ (ለታላቁ መሪ) ባላቸው ቅርበትና ርቀት ሰዎች በህግ የሚጠየቁበትና የማይጠየቁበት፣ የመንግስት ሃብት በተጠናና ዘለቄታዊ ልማት በሚያመጣ ሳይሆን ከ "ታላቁ መሪ" ጋር አብረው የነበሩት የህውሓት አመራሮች ለማስቀናት፣ በለጥኳችሁ ለማለት በሚመስል መልክ 4 እና 5 ፕሮጀክት የሚያሰራ ሃብት በጭፍን ይፈስ ጀመረ፡፡ መንገድ፣ መስኖ፣ መብራት፣ቴሌኮም፣ትምህርትና የመሳሰሉት ፕሮጀክቶች የሰው ኃይልና እውቀትን መሰረት ባደረገ መንገድ ሳይሆን በገንዘብ ኃይል ብቻ እየተሰሩ አገሪቱ ያወጣችውን ያህል ሳይሆን ካወጣችው ገንዘብ እጅግ ያነሰ አፈፃፀም እያሳየች ራሷን ወደሚያደቃት ወጪና ብድር እየተዘፈቀች ሄደች፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ ህውሓት ላይ የመግደል ሙከራ አድርገው ህውሓት በጠና ታማ አልጋ ላይ እያለች እሳቸው በተፈጥሮ ቀድሞው ሞቱ፡፡ የአቶ መለስ ዜናዊ ቀድሞ መሞት በኢትዮጵያ ፖለቲካ እጅግ ፈታኝ፣እውነታውን ማወቅና ድፍረት የሚጠይቅ ሁኔታ ፈጥሮ አሁን ወዳለንባት ኢትዮጲያ ወደ መኖር ወይም ወደ መበታተን አደጋ መንታ መንገድ ላይ አድርሷታል፡፡

## <u>የትግራይ የበላይት የሚለው አስተሳሰብ ከየት መነጨ?</u>

በ1983 ዓ/ም ኢህአዴግ ከነበረው ተዋጊ ኃይል 90% ታሪካዊ አጋጣሚ የፈጠረው የህውሓት ታጋይ ነበር፡ ይህ በቁጥር ወደ 130,000 የሚጠጋው ተዋጊ ኃይል በህውሓት አመራር የፖለቲካ ትምህርት የተማረ እንዲሁም አመራሩን እንደማይሳሳት፣ ሙስናና ጥቅማጥቅም የማይነካው ስለ ህዝቡና ስለአላማው ታማኝ የሆነ አመራር ነው ብሎ ያምን ሰለነበረና ከዚህ እምነቱ በተፃራሪ በኑሮ እና አኗኗር ላይ ለውጥ ሲያይ ጥያቄዎች ሊያነሳ እንደሚችል የህውሓት አመራር (ልሂቅ) አስቀድሞ ገብቶት የነበረ ይመስላል፡፡ በዚህም መሰረት በ1984 ዓ/ም የማመጣጠን አጀንዳ አንስቶ ስጋት ሊሆኑ ይችላሉ

ተብለው የሚገመቱትን ከሰራዊቱና በተለያዩ የድርጅቱና የመንግስት መዋቅር ይሰሩ የድርጅቱ አባላት፣ የሚኖረውን የፖለቲካ አካሄድ በአርትኦ አና በሂስ ሊያዩ የሚችሉቱ ላይ ያነጣጠረ ግምገማ በ1985 ዓ/ም ክረምት ተደረገ፡፡ በዚህ የግምገማ ወቅት አመራሩ ራሱን የመላእክት ስብስብ እንደሆነና ሌላው አባልየስህተቶች ሁሉ ምንጭ፣ አስተሳሰቡ የዘቀጠ፣ አመራሩን የሚያማ እንደሆነ ግምገማውን አወረደልን፡፡

በወቅቱ በሰራዊቱ ውስጥ ከነበረን አባላት በተለይም ከሻለቃ አመራር በላይ በጦር ሃይሎች መሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰብስበን የማእከላይ ኮሚቴው ግምገማና ውሳኔ ቀረቦልን አስተያየት እንድንሰጥበትና ድክመታችንን እንድንናዘዝ ተጠየቅን፡፡ እኔ እድሜየን ሙሉ አደንቃቸውና አከብራቸው የነበሩ የቅርብ አለቆቼ ሳይቀሩ በስብሰናል፣ ሸተናል፣ አልሰራንም ይቅርታ ይደረግልን በማለት ራሳቸውን ለአመራሩ (የልሂቁ) ተግዥነታቸውን አረጋገጡ፡፡በጊዜውከነበረው የህውሓት ተዋጊ ሃይል ላይ እንኳንም ተቀንሶበት እስከ 200,000 ወታደር ቢጨመር ኢትዮጵያን የሚያክል ትልቅ ሃገር ሰላሟን ማረጋገጥ ትልቅ የቤት ስራ ነበር ፡፡ ለዚህም ነው ከአራት አመት በኋላ በ1990 ዓ/ም በኤርትራ ተወራ አስቅድማ ልትከላከለው ትችል የነበረውን ጦርነት ውስጥ ተዘፍቃ መከፈል የማይገባውን መስዋእትነት የከፈለችው፡፡ ነገር ግን ለህውሓት ልሂቅ ትልቅ ስጋት የነበረው በተነፃፃሪ የሚያውቀውና ጥያቄ ሊያነሳ የሚችለው አብሮት እያታገለ የመጣው ታጋይ ስለነበረ የዚህ ታጋይ ፖለቲካዊ ስብእና ማኮሰስ፣ ከአስጊነት ደረጃ ማውረድ አጅግ ቀዳሚ አጀንዳ አድረጎ ተንቀሳቀሰበት፡፡ በዚሁም የትግራይ ተወላጆች በሰራዊቱ ውስጥ ስለበዛን፡-

1. በመልሶ ማቋቋም ሰበብ ቁጥሩን መቀነስ
2. በዚህ የመልሶ መቋቋም ሰበብ በተቻለ መጠን ጥያቄ የጠየቁ፣ ሊጠይቁ የሚችሉ ራሳቸውን ማስገዛት የማይፈልጉ አባላትን ኢላማ ማድረግ
3. በመልሶ ማቋቋም የሚወጣው አባልም በፍጥነት እዳይቋቋም ብዙም ከድህነትና ከልመና እንዳይርቅ በማድረግ በሰራዊቱ ውስጥ የቀረውን አባልቢወጣ የሚገጥመው እጣ ፋንታ ድህነት ነውብሎ ራሱን አስገዝቶ በታማኝነትና በፍርሃት አገልጋይ እንዲሆን የሚያደርግነበር፡፡

በዚህ ምክንያት በመልሶ ማቋቋም (demoblization) ከሰራዊቱ የተቀነሱ አባላት ወደ ዳንሻ ተውስደው ምንም መሰረተ ልማት በሌለበት እንዲሰፍሩ ተደረገ፡ ወደ ዳንሻ መሄድ ያልቻሉት ደግሞ በነብሰወከፍ 5000 ብር እየተሰጣቸው ተሰናበቱ፣ ትምህርት የመማር ፍላጎት የነበረን እድለኞቹ (እንደኔ አይነቶቹ) በአንዳንድ አመራሮች አዘኔታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህራታችንን ምንም የሚከፈልም የምንከፍለውም ሳይኖረን ተማርን፡፡ ነገር ግን በግምገማው ወቅት ያነሳናቸው ጥያቄዎች እያደኑን እየተከተሉን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታችንን ጨርሰን ዩኒቨርሲቲ የመግባቱ እድል አገኘን፡፡

ወደ ተነሳሁበት ለመመለስ የትግራይ የበላይት የሚለውን ሃሳብ በመጀመሪያ ማንፀባረቅ የጀመረው አባላቱን ማሸማቀቅ የፈለገው የህውሓት ልሂቅ ነው፡፡

ይህ የትግራይ የበላይነት አስተሳሰብ እንደቁስል እያመረቀዘ የትግራይ ህዝብና በንቃት በኢትዮጲያ ፖለቲካ ሊካፈሉ የሚችሉትን የአካባቢው ተወላጆች ራሳቸውን ከህውሓት አመራር ውጭ የሚያዩበት ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እንዳይኖራቸው ያለመታከት ተሰርቶበታል፡፡ በ1993 ዓ/ም በነበረው የህውሃት አመራር መሰንጠቅ የፖለቲካ ስልጣኑን የተቆጣጠረው የአቶ መለስ ዜናዊ (ልሂቅ) ጥያቄ መጠየቅናህወሓት ወደነበረበት የቡድን አመራር ይመልስ ሊሉ ይችላሉ የተባሉትን ከፍተኛ መኮንኖችና በተለያየ መስሪያ ቤቶች ይሰሩ የነበሩ የህውሓት የከፍተኛ አመራር አባላትን ማሽማቀቅ የተጀምረው፡፡ በሰፈሩት ቁና መሰፈር እንደሚባለው በ1985 ዓ/ም ግምገማ ጊዜ ገምጋሚ የነበሩ ጀኔራል መኮንኖች በ1993 ዓ/ም ክፍፍል ጊዜ ጎራ ተለይቶላቸው የቀደሙቱ እጣፈንታ የትግራይ የበላይት አለ ተብው ተሰናበቱ፡ የዚህ አቋም ቀንደኛ አራማጅም በብቸኛ ልሂቅነት የወጡት የህውሓት ሊቀመንበር ነበሩ፡፡

## <u>የትግራይ የበላይነት ወይስ የህውሓት የበላይነት?</u>

የህውሓት የበላይት ለማለት ከሆነ ኢህአዴግ የውስጥ መድረኩን ይገምግም የህውሓት የበላይነት የትግራይ የበላይነትንእያሳይም፤ ህውሓትን የሚመሩት ሰዎች ህውሓትን እንዲመሩ የመረጣቸው የህወሓት አባላቸው እንጂ የትግራይ ህዝብ አይደለም፡፡የህውሓት ድርጅት የሆነው አባላቱን ሰብስቦ እንጂ የትግራይ ህዝብ አማክሮ ስላልሆነ የትግራይ ህዝብ አይመለከተውም፡፡ በነገራች ላይ ህዝብን በአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ለመገደብ ወይም ከአንድ ፓርቲ በላይ አይወክለውም ብሎ ማሰብ ወይንም ያው የትግራይ ህዝብና ህወሓት አንደ ነው ብሎ መግለፅ ፀረ ዲሞክራሲዊ ነው፡፡በተለይም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ወይምበመደብ የተከፋፈለን ህዝብ በአንድ አስተሳሰብ ለማጨቅ መሞከር ፀረ ዴሞክራሲም ፀረ ልማትም ነው፡፡

ህዝብ የአስተሳሰብ ምንጭ ነው ስለሆነም ከህዝብ የሚወጡ ብዙ አስተሳሰቦች ህግ እና ስርዓት ተበጅቶላቸው በርከት ያሉ የፖለቲካ አደረጃጀቶችን ይፈጥራሉ እነዚህ አደረጃጀቶች አቋማቸው በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ እየገለፁ የሚደማመመጥ እና ዴሚክራሲያዊ ባህል ያለው ህዝብ ይፈጥራሉ በሌላ አባባል የሰለጠነ ማህበረሰብ የሰለጠነ ፖለሪካዊ ስርዓት ይኖራቸውዋል፡፡ በዚህ መሰረት ህውሓት በትግራይ ውስጥ ሊወክል የሚችለው በአንድ ወቅት አንድ አይነት አስተሳሰብን ወይንም አንድ አይነት አማራጭን ብቻ ነው፡፡

አንድ ህዝብ በሌላ ህዝብ ላይ የበላይነት አለው ሊባል የሚችለው ምን ሲሆንነው፡፡

1. ቋንቋውን በኃይል በሌላው ህዝብ ላይ ከጫነ
2. ባህልን እና ሃይኖቱን በሌላኛው ህዝብ ላይ የሚጭን ከሆነ
3. ህዝቡ ራሱን የማስተዳደር መብቱን ነጥቆ በመጤ ሰዎች (ከጨቋኙ በመጡ) እንዲተዳደር ቢያስገድድ

4. የህዝቡን ተፈጥሮአዊና ሰብአዊ ሃብቱን ሲነጥቀው እና የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ የዘረዘርኳቸውን የበላይነት መገለጫዎችን በሌላ ህዝብ ላይ የፈፀመ ህዝብ በዚህ አለም አልተፈጠረም፡፡ የበላይትን የሰበኩ ያስፋፉና የተገበሩ ገዥዎች እንጅ ህዝቦች አይደሉም፡፡ ህዝብ በራሱ ላይ እንዲደርስበት የማይፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አያደርስም ቋንቋውን መነጠቅ ስለማይፈልግ የሌሎችን አይነጥቅም፣ ባህሉን ማጣት ስለማይፈልግ የሌሎች ህዝቦችን ባህል መንጠቅ ላይ አይሰማራም፣ ራሱን ከማስተዳደር ውጭ ሌሎችን የማስተዳደር ፍላጎትም ምኞትም የለውም ስለዚህ አስተዳደሩን በሌሎች ላይ አይጭንም፡፡

አውሮፓውን ቅኝ ግዛትን አስፋፍተው የሰው ሃገር የነጠቁት፣ የህዝብ ባህልና ቋንቋ ያጠፉት ህዝብን በጅምላ ፍጅት የፈፀሙት የአውሮፓ ህዝብ ይሁንታን ጠይቀውና የአውሮፖን ህዝብ ሂዱና ሌሎች ህዝቦችን አጥፉልኝ ስላቸው አይደለም፡፡ ነገር ግን በስመ አገርናአርበኝነትከሌላኛውን ህዝብ አናክሰው በጠላትነትና በቂም እየተያየ ወደ መሰረቱት እጅግ የቆሸሸ ስርዓታቸው ፣ በማያባራ ዘረፋ ላይ፣ ህዝብ መግደል ላይ የተሰማራ መንግስታቸውን ህዝብ ገልመጥ በሎ እንዳያይባቸው ለማድረግና የትልቅነት አታሞ እየመቱ ከሌላው ህዝብ የተሻለ ሃያል እንደሆነ እየሰበኩ ዘልአለማዊ ገዥነታቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ አለም ላይ እየዞሩ የለኮሱትን እሳት የሚፈጃቸውን ህዝቦች ምስል እያሳዮ ሲያስፈልግም ውስጣዊ ሽብር እየፈጠሩ ግዛታቸውን ከትውልድትውልድ ያስተላልፋሉ፡፡ ስለዚህ ጥላቻ የህዛቦች አይደለም የበላይነትና የበታችነትም የህዝቦች አይደልም የገዥዎች እንጂ፡፡

የትግራይ ህዝብ በማንም ላይ የበላይ ሊሆን አይችልም ነገር ግን ስልጣናቸውን አላግባብ የተጠቀሙ የህውሓትም ይሁኑ ሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የሚፈፅሙት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ብልሹነት እንዳይታወቅባቸው ኑሮውን ለማሸነፍ ያለ እረፍት የሚሮጥን ህዝብ እየተከተሉ ጣት ይቀስሩበታል፡፡ በዚህ ግንባር ውስጥ የስልጣን ጥመኞች፣ ሙሰኞች፣ ጠባቦች፣ ትምክህተኞችና ሌሎች ግንባር ፈጥረው በታሪካዊ አጋጣሚ የነበረውን የትግል ተሳትፎ ሰበብ በማድረግ የጥፋታቸው መሸፈኛ የትግራይ ህዝብ ላይ መዝመት ሆነ፡፡ አታገልልሃለሁ የሚለው ሀወሓትም ከጅምሩ ጀምሮ አሳት በማቀበልና የትግራይ ህዝብ ህወሓት ከሌለ መኖር አልችልም የሚል አስተሳሰብ ይዞ በስጋት እንዲኖርና የህወሓት ጥገኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ባለፉት ስርአታትአፄዎችና ገዥዎች በዘረፉትና በበሉት የአማራ ህዝብ ተከሳሽ ለማድረግ እንደዘመቱበት ሁሉየአሁኑቹ የዘረኝነት ካድሬዎችየነፍጠኛ ስም ሲጠራ ህዝብንና ነፍጠኛን አንድ ለማድረግ ሲሰብኩ የጠባብነት ፖለቲካ አራማጆች መደበቂያ ሲያደርጉ እንደሚዉሉትና ህዝብን ዘርፈውና አፈናቅለው ሲያበቁናራሳቸውን ሰማይ ጥግ ያደረሱ ዲታ ፖለቲከኞች "የህዝቤ ክብር" በሚል መፈክር ይሸፈናሉ፡፡

ለማጠቃለል የትግራይ የበላይነትን ዘፈን ደራሲዎቹም፣ አዝማሪዎችም ተቀባዮቹምባጠቃላይ ሙሉ ባንዱ አሁን ያሉ ገዥዎችና ጀሌዎቻቸው እንጅ ማንም ህዝብ አይደለም፡፡ እንደ ህዝብ የሌለው ህዝብ የበላይም የበታችም አይደለምና፡፡

## ኢህአዴግና የመርህ መዘበራረቅ

በዘመነ አቶ መለስ ዜናዊ ህውሐት/ ኢህአዲግ የመንግስቱ አንኳር ነው የተበለ የኢትዮጵያ መንግስት የወያኔ መንግስት እየተባለ ሲጠራ የኢትዮጵያ መንግስት የሁላችን መንግስት ነው እኛ በጥቂቱ የክልላችን ህዝቦች በህገመንግስቱ መሰረት የምናስተዳድርና በፌዴራል መንግስቱ ውሰጥ ሊቆጠር እና ሊታይ የሚችል ህልውና እና ባለቤትነት ያለን የፖለቲካ ድርጅቶች ነን ብለው አንዳቸውም የኢህኢዲግ አባል ድርጀቶች አደባባይ ላይ ወጥተው መንግስታቸውን ሲከላከሉ አላየንም፡፡ እንዳውም አንዳንድ የክልል መሪዎች ሳይቀሩ የጥፋቶች ሁሉ የሚከሱትና የሚወነጅሉት ህውሓትን ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ በኔ እምነት መሰረት የሌለው ነው አልልም ምንም እንኳን ከሃላፊነት ለመሸሽ እና ግዴታን ላለመወጣት ለሁሉም ነገር ተጠያቂነት አለበት ባልልም በዚህ ፅሁፍ መጀመሪያ አካባቢ እንዳነሳሁት የአንድ የተሳካለት ድርጅት መገለጫ አድርጌ ከምወስዳቸው አስተሳሰቦች ውስጥ ድርጅታዊ ርእዮት አለምመፍጠር የቻለ የድርጅት (ልሂቅ)የተሳካለት ከሚባሉት ውስጥ ነው ብየ ነበር፡፡ በዚህ መሰረትም የአብዮራዊ ዴሚክራሲ ፈጣሪ እና ባለቤት ህውሓት ነው (የህውሓት ልሂቅ ቡድን በኋላ ብቸኛው አቶ መለስ ዜናዊ ናቸው)፡፡ ቡድን የነበረው የህውሓት ልሂቅ በብቸኛው አቶ መለስ ዜናዊ ሲተካ ህውሓት ብሎም አቶ መለስ ዜናዊ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ርእዮት አለምን ይሁን ልማታዊ ዴሞክራሲዊ መንግስት የመንግስት ቅርፅ ባለቤት ስለሆኑ የአስተሳሰቡ ባለቤት ቢወቀሱ ከእውነታው እምብዛም የራቀ ሊሆን አይችልም፡፡

ሰለሆነም እኔም ህውሓት ላይ የበለጠ ትኩረት የማደርገው ህውሓት የልሂቁ ንብረት በመሆኑ ይህ ልሂቅ የድርጅቱን ደንብና ስርዓት እና ድርጅቱ የሚመራበትን ርእዮቶ አለም በባለቤትነት ስለያዘነው፡፡

ኢህአዴግ ለሚከተለው መርህ(መስምር) ሲሳካ እንደሚሞገሰው ሁሉ ሲዘበራረቅም ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት ባይ ነኝ፡፡ ከዚህ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ሊድን የሚችለው አስተሳሰቡን እና ርእዮት አለሙን ሃገራዊ አቋም በማድረግ ባለቤትነቱን ከልሂቅ ወደ ተቋማትና ህዝብ ማስተላለፍ ሲችል ብቻ ነው፡፡ የህውሓት አስተሳሰቦች የኢትዮጵያ መንግስት የአስፈፃሚው ምርምርና ስርዓት ተቋማት በባለቤትነት ካልተመራመሩበት፣ካላሻሻሉት፣ካልገመገሙት እንዲሁም ካላሳደጉት በስተቀር ንብረትነቱ የህውሓት በተለይ የልሂቁ ነው፡፡ ይህ የባለቤትነት ሁኔታ ስላልጠራና ባለቤትነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ፍኖተ ካርታ (road map) ስለልነበረው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ርኢዮተ አለምም ይሁን ዲሚክራሲዊ ልማታዊ መንግስት የመንግስት መልክአ አወቃቀር ከጠጣር ቃላትነትና ከተቀዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መቀለጃ ቃላት በዘለለ በተቋም መርህነት የማናገኛቸው አሁን ደግሞ የመንገስቱ ከፍተኛ ሚኒስሮች ሳይቀሩ ከቃሉ በስተቀር ሊያብራሩት የማይችሉት ወሬ ሆኖ ቀርቷል፡፡

ከፍተኛየአቋም መዘበራረቅና የመልማት አቅጣጫ መደበላለቅ በኢህአዲግ በኩል እንዲታይ ምክንቱም፤ የፈጠሩት ባለቤቱ በሂወት ከተለዩት በኋላ የሚታዩ አለመጥራቶችን ገምግሞና በሰነሃሳቡ

መሰረት ስርዓቱንና ህገመንግስቱን ሳይሸራረፍ ማስተካከል የሚያስችል ተቋም አለመኖሩ ነው፡፡ ለምሳሌ አቶ መለስ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አማካኝነት የኢትዮጵያ ውስጥ ሊረጋገጥ የሚችለው ብለው በሁሉም መድረኮች ይሰብኩ ነበር፡፤ እንደማስታውሰው በየአመቱም በአነስተኛና ጥቃቅን የተደራጁ ወጣቶችን ወደ ኢንዱስተራላዊነትደረጃ ተሸጋግረዋል እያሉ ይሸልሙ ነበር፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ወደ አለማቀፍ የፋይናንስ ገበያ መቸም ቢሆን አትገባም ብለው የኢትዮጵያ ጀልባ አገር ውስጥ ካለን ወንዝ አትወጣም ብለው በምሳሌ ያቀርቡ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሳቸው ሞት በኋላ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ እድገት በዋናነት በኢንዱስትሪ በበለፀጉ ከውጭ ቀጥታ በሚመጡ አመራች ኢንዱስትዎች (FDI) ነው ፤የቴክኖሎጂ ሽግግርና እድገት የሚረጋገጠው ለዚህም አገሪቱ የተሟሉ ኢንዱስትሪያዊ ፓርኮችን በመገንባት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ አለባት አነስተኛና ጥቃቅኖች ለነዚህ ፓርኮች በመጋቢነት ወይም የአገር ውስጥ ገበያ በመሸፈን ሚና ይኖራቸውል እንጂ የቴክኖሎጂና የእውቀት መስፈንጥሮች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በሌላኛውም በኩል ከአቶ መለስ ዜናዊ ሞት በኋላ የኢትዮጲያ መንግስት መጠኑ አነስተኛ ቢሆንም እንኳን ለኡአላዊ ቦንድ(Sovereign bond ) ለገበያ አቅርቦ አቶ መለስ ዜናዊ አንገባበትም ያሉትን አለማቀፍ የፋይናንስ ገበያ ጣቶቹን አስገብቷል፡፡

በዋናነት ግን በሁሉም የልማት አቅጣጫዎች እና ዘርፎች የቅደም ተከተልና የመዋቅር ችግር ይታይባቸዋል የዚህ መንስኤው ተቋማዊ ባለቤትነት የሌለው ርእዮተ አለም እና የመንግስት አቅጣጫ ነው፡፤ በኢትዮጵያ ደረጃ የሚወጡ የፖሊሲ ሃሳቦች በተቋም እየተጠኑ መንግስታዊ (ሃገራዊ) ባለቤትነት በሃገር ደረጃ የሚተዳደሩ ስላልሆኑ በዘፈቀደ የሚመሩ ስለሆኑ በፈፃሚ የመንግስት ተቋማት እንኳን መናበብ የለም ምናልባትም የተፈፃሚነት እድላቸውን እየቀጨጨ ለመሄዱ አንዱ ምክንያት ነው ባይ ነኝ፡፡

## ኢህአዴግና የተቀዋሚ ድርጅቶች

በመሰረታዊ መነሻው ኢህአዴግና የተቃዋሚ ድርጅቶች አንድ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ተቃዋሚ ድርጅቶች ራሳቸውን ያደራጁት የኢህአዴግ ስህተቶችን ለመንገርና ኢህአዴግ እንዲስተካከል ለመምከር እንጂ አማራጭ የፖለቲካ መርህ/ርእዮተ አለም ሰላላቸው አይደለም፡፡ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በመግቢያየ እንዳልኩት፤ ህግና ስርዓቱን መቆጣጠርና የርእዮተ አለም ባለቤት የሆነ ልሂቅ መፍጠር አለበት ይህ ልሂቅም የራሱ ፖለቲዊ ስብእናን ስለሚያንፀባርቅ ተወዳዳሪ ነው፣ይለያል፣ በሌሎች ድርጅቶች ስህተት ተመስረቶ አይደራጅም አማራጭ ርእዮት አለሙን ለማስፋፋት ይሞክራል እንጂ በገዥው ፓርቲም ወይንም በአጎራባች ድርጅት ቀጥተኛ ተፅእኖ ስር አይወድቅም ስለሆነም የተቀናቃኝ ድርጅቱን ድክመት ላይ ሙሉ ጊዜውን አያጠፋም ተቀናቃኝ ድርጅቱ የሚከተለውን ርእዮት አለም እንዴት እየተጠቀመበት እንደሆነ ይመረምራል የራሱ ርእዮት አለም ተመሳሳይ ስህተቶችን ሳይፈጥር እንዴት ሊያድግ እንደሚችል ያጠናል ሳይንሳዊ ግምገማ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ከገዥው የፖለቲካ ድርጅት በሚመጣ ፍርፋሪ ድክመቶች ራሱን አያኖርም ይልቁንም

ራሱን እጩ መንግስት አድርጎ የበሰለ እና የተሻለ አማራጭ መንግስት እንዴት መሰረት እንደሚችል ፍኖተ ካርታውን ይሰራል፡፡

በኢትዮጲያ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች አሁን በያዙት መንገድ መቸም ቢሆን ከገዥው ፓርቲ ተፅእኖ ነፃ ሊሆኑ አይችሉም አብዛኞቹ ኢህአዴግ ላይ የሰፈሩ ጥገኛ ተባዮች መስለው ይታዩኛል፡፡ የራሳቸው የሆነ ልሂቅ የላቸውም፣ርእዮት አለም የላቸውም ስለዚህ የኢህአዲግን እንከን ሲለቅሙ ይውላሉ፡፡ በኔ እምነት ኢትዮጲያ ውስጥ በለዘብተኝነትም በአክራሪነትም ኢትዮጲያ ውስጥ አማራጭ ፖለቲካ ድርጅቶች አልተፈጠሩም አሁን ባለው አካሄድ ሊፈጠሩ አይችሉም፡፡

## ኢህደዴግ በህገመንግስታዊ ስርዓት ማፍረስ ስራ መጠመድ

ኢህአዲግ በባለቤትነት የያዘውንና ከፍተኛ መስዋእትነተ ተከፍሎበት የተገኘውን ህገመንግስ በማፍረስና በመሸራረፍ በአክራሪነት እና በአሸባሪነት ከተፈረጁ ድርጅቶች ይበልጣል፡፡

ህገ መንግስቱን ኢህአዲግ በድርጅት ደረጃ ያስከብራል ተብሎ በተቀመጠ ህገመንግስታዊ ተቋም ያለማመነታት ሲያፈርሰውና ሲንደው ይውላል፡፡ ኢትዮጲያ የብዙ ብሄርና ብሄረሰብ አገር ናት፡፡ እነዚህ ህዝቦች በከፋውም በለማውም ወቅት የዚህች አገር ጀማሪም ገንቢም ሆነው ባርነትና ጭቆናን ችለው መንግስታታ ተነሱ ታጠቁ ለዚች አገር ሙቱ ሲሏቸውሲሞቱ ነገር ግን ከጦርነቱና ከአገር የመጠበቁ ሃላፊነት ሲመለሱ በአድሏዊና ፍርደ ገምድል አሰራራቸው እንደገና መቀመቅ ሲከቷቸው ከድህነትም ወደ ከፋ ድህነት ሲዘፍቋቸው ኖረዋል፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ በላያቸው ላይ የተጫነውን አስከፊ ስርዓት ያወግዙ እንደሆን ነው እንጅ ሌላኛውን ህዝብ ጠላቴ ነው፣ ካላጠፋሁት በሚል ገዥ መደቦች ከሚናገሩት ቋንቋ ጋር የተገናኘን ህዝብ በጥፋተኝነት ወንጅለው የዘር ማጥፋት ዘመቻ ውስጥ ገበተው አያውቁም መቸውንም፡፡ ነገር ግን በጠባብ ጥቅማቸው ውስጥ ታጥረው የተቀመጡ ገዥዎች ግን የዚህ ክፋት ምንጭ የጥፋቱ ተጠያቂ ራሳቸውን ሳይሆኑ ይህኛው ቡድን ወይም ያኛው ቡድን ከመጣበት አካባቢ ህዝብ ጋር በማገናኘት ላይ ተጠምደው በህግ ደረጃ ያስቀመጡትን በአደባባይ ያወጁትንና የፃፉትን መተዳደሪችን ነው የሚሉትን ህገመንግስትም ይሁን ከዛም አልፈው የህብረተሰቡንየአብሮነት ባህል ሲጥሱና ሲያፈርሱ ይውላሉ፡፡ ሰው አይሸጥም አይለወጥም ብለው ህገስርዓታቸው ላይ ያሰፈሩት አፄዎች ሰው ሲሸጡና ሲለውጡ ይውሉ ነበር፡፡ “ያለምንም ደም ኢትዮጲያ ትቅደም”ያሉን ገዥዎች የደም ጎርፍ አሳይተውን በጠራራ ፀሃይ የሰው ልጅ እንደ ነፍሳት ሲበጠረቁ የተቀንተቀን ኑሮችን መስሎን እስክንቀበለው ድረስ አስለምደውን ነበር፡፡ ህግ ሌሎችን መቅጫ ብቻ ነው ብለው ስለሚያምኑ በየቀኑ ይጥሱታለ፤ ያፈርሱታል ደስ ያላቸውን ያደርጉበታ፡፡

ልክ እንደ ቀደምቶች ኢህአዴግና ኢህአዲግ መራሹ መንግስት እገዛበታለሁ ያለውን ህገመንግስቱን በድርጅት ደረጃም በግለሰብ ደረጃ ሲያፈርሰውና ሲንደው ይውላል፡፡ በሌሎች አካላት የአገሪቷ

ህግመንግስት ሲናድ ለስልጣን የሚጠቅም እስከመሰላቸው ድረስ ወይም ዝምታን ወይምንም በአይዞህ ባይትን ይጨምሩበታል፡፡

በኢትዮጲያ ህገመንግስት የሁሉም ኢትዮጵዊ ሰብአዊና ዲሞክራሲዊ መብት መከበር እንዳለት በአፅንኦት ያስቀምጣል፡፤ የአህአዲግ ባስልጣናትና በባለስልጣናቱ ስር የሚሽከረከሩ ተቋሞቻቸው ሰውን ያለበደሉ ስለጠሉት ወይንም ስለጠየቃቸው ብቻ ፖለቲካዊ ስም ይለጥፉበታል፣ይዝቱበታ፣ የመስራትም ሆነ የመዘዋወር መብቱን ይነፍጉታል፣ ጋዜጣ ላይ ቢፅፍ ወይንም አቋሙን ቢገልፅ ያስፈራሩታልበሰላም የመኖር ሰብአዊ መብቱን ደስ እንዳላቸው ያጨማልቁታል፡፡ የሚጠይቃቸው የለም ሲጠየቁ ግን ፀረ ህዝብ ነው ይሉታል ራሳቸውን ህዝብ አድርገው ለህዝብ የተሰጠውን ህገመንግስታዊ መብት ለራሳቸው ወስደው ከህዝብም ከህግም በላይ ሆነዋል፡፡

አሁን በእውን የምናየው ይህ ህዝብ ከዚህ አካባቢ ይውጣልን ያኛው ህዝብ ከዛ አካባቢ መውጣት አለበት ከዚህ አካባቢ የመጡት ሰዎች ወረሩን እየተባ ላለፉት 26 አመታት ሲሰበክ ኢህአዲግ ወይ እሳት አቀባይ ነበር ወይንም እንዴት ለስልጣኑ እንደሚጠቀምበት ብቻ ያስብ ነበር፡፡ ከላይ ለጠቀስኩት ዝርዝር ሃሳብ ማሳያ ሊሆኑ የሚችሉትን ምሳሌ ልጥቀስ፡፡

ከላይ በተደጋጋሚ እንደገለፅኩት በኢህአዲግ አባል ድርጅት መሪዎች እና በቀድምት ስርዓት አራማጅ ቅሪቶች የትግራይ የበላይነትአለ፤ ትግሬ ቅኝ ገዛን፤ ሁሉም ነገር ወደ ትግራይ እየተሰጠ ነው ወዘተ እየተባለ ሲሰበክ እና በዚህ ተግባርም ዜጎች ተዘዋውረው የመስራትና ሃብት የማፍራት ህገመንግስዊ መብታቸው ሲጣስ ኢህአዲግ እንደድርጅት የየአካባቢው አስተዳደር እንደ ተቋም የክልል መሪዎች እንደግለሰብ የሚሳተፉበት ነበር፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢህአዲግ ስራ አስፈፃሚ የትግራይ የበላይነት መኖሩን እና አለመኖሩን ለማጣራት ኮሚቴ አቋቋሞ ፎቅ ሲቆጥር እንደነበር ስሰማ ድርጅቱ ምን ያክል ከመርህ እና ከህግ ወጥቶ ወደ ተራ ስራና የመንደር አሉባልታ መግባቱን ማሳያ አደርጌ እወስደዋለሁ፡፡

በተጨማሪም በደቡብ ኢትዮጲያ በጉራፈርዳ የአማራ ተወላጆች ናችሁ የተባሉ ንፁሃን ዜጎች ሲገደሉና ሲፈናቀሉ ቀድሞ ለመድረስና ለምን ተፈናቀሉ ብሉ በድርጅት ደረጃ ከዲኢህዴን አመራሮች ጋር የተነጋገረውና የተወያየው ብአዴን ነበር፡፡ አሁን በቅርቡም በመቱ አካባቢ በዜጎች ላይ በደረሰው መፈናቀልና የዘር ማጥፋት ተግባር የመንግስት ህዝብ ግንኙነት ኃላፊውን ልኮ የተነጋገረው የአማራ ክልላዊ መንግስት ስለ አማራ ተወላጆች ጉዳት ነበር፡፡ እነዚህን ሁለት ተግባራት ብቻ በመውሰድ እንዴት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችህጋዊ ስልጣን የሰጣቸውን ህገመንግስታዊ ስርዓት እንደሚያፈርሱት ማሳያዎች ናቸው፡፡

መጀመርያ ነገር በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ከየተኛውም ክልል ይሁን ብሄር መጥተው በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንዲሰሩ ህገመንግስታዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩ የማድረግ ኃላፊነት የዛ የሚኖሩበት አካባቢ መስተዳድር ኃላፊነት ነው፡፡ በሰላም የመኖር መብታቸውን የመጠበቅ ጉዳት በሚደርስበት ጊዜም ለሁሉም ህዝቦች በእኩል የማስተዳደር ሃላፊንቱ መሆኑ በህገመንግስቱ መሰረትም ፖለቲካዊና ሰብአዊ

መብታቸው አለመጣሱን እንዳይጣስም ያለምንም ልዮነት የማገልገል ግዴታ ያለበት የአካባቢ መስተዳደሩ መሆኑ በህገመንግስቱ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ስለዚህ ኃላፊነቱ ጉዳት የደረሰበት ዜጋ ብሄር እየታየ ወደ የክልሉ ባስልጣናት ወይንም እወክልሃለሁ ወደሚሉት ድርጅቶች የተሰጠ አይደለም፡፡ በእንደዚ ላለ ኢ-ህገመንግስታዊ ግንኙነት መሰረት ካየነው አንዳንዱ ክልል የኔተወላጅ ወይን በኔ ብሄር የሚጠራ ሰው አለበት ባለው አካባቢ ሁሉ ቆንስላ ፅ/ቤት ወይንም ኢምባሲ ማቋቋም ሊኖርበት ነው፡፡ በሌላ በኩልም የአካባቢው መስተዳድር ግዴታውን አልተወጣም ካለ እና ጉልበተኛ ነኝ ብሎ ካሰበ ታጣቂ ሃይሉን አሰማርቶ የኔን ሰዎች የኔን የብሄር አባላት ለመታደግ እዋጋለሁ ሌለን ነው፡፤ ይህ ወደ እርስ በርስ ጦርነት የመግቢያ በር እየተንኳኳ ያለው በኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና የክልል መንግስታት ነው፡፡

አንድ ሰውም ይሁን ቡድን በሚኖርበት አካባቢ በደል ቢደርስበት የመጀመርያው ኃላፊነት የአካባቢ መስተዳድር ነው፡፡ ሲቀጥል የክልል መስተዳድር ኃላፊነት ነው በነዚህ አካላት ችግሩ ካልተፈታ ግን የፌዴራል መንግስት ኃላፊነት ነው፡፡ ሰው ተበደለብኝ የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የክልል መስተዳድሮች ጉዳይ በፍፁም አይደለም፣ ህገመንግስታዊ ስርዓቱም አይፈቅድም፡፡

በቅርቡ የኦህዴድ ማእከላይ ኮሚቴ ተሰብስቦ የኦሮምያ ተወላጅ ተማሪዎች ከኢትዮጲያ ሶማሌ ዮኒቨርስቲዎች በኦሮሚያ አካባቢ ወዳሉ ዮኒቨርስቲዎች አዘዋውራለሁ ማለቱንና የትምህርት ሚኒስቴርም ተግባራዊ ማድረጉ ለሁላችንም ዜጐች ግልፅ ያለ መልእክት አስተላልፏል የፌዴራል ስርዓቱእነደማይሰራና የዜጎችን አብሮነት እና ተዘዋውሮ የመኖርና የመስራት ህገመንግስዊ መብት በግልፅ መፍረሱን እንዲሁም በአገሪቷ ክልሎች መብት አለመኖሩን ወደየ ክልላችን እንድናማትርና የጋራ አገር እንደሌለን አሳውቆናል፡፡ ከላይ የገለፅኳቸው ምሳሌዎች እጅግ ጥቂቶቹ ናቸው በየቀኑ የመስራት መብትን፣ ከባንክ ብድር የማግኘት መብትን፣ ንብረት የመግዛት መብትን፣ ቋንቋ የመጠቀም መብትን እየተነፈገና በበሄሩ ምክንያት በትልልቅ ባስልጣናት እንዲሸማቀቅ እየተደረገ የሚውለው ዜጋ ህዝብ ይቁጠረው፡፡

ለማጠቃለል ለዚህ ህገመንግስት መጣስ እና ህገመንግስዊ ስርዓት የማፍረስ ተግባር በግምባር ቀደምትነት ተጣያቂው ኢህአዴግ፣ የኢህአዴግ አባል ድርጅቱች እንዲሁም የኢህአዴግ ሹማምንት ናቸው፡፡

## <u>ኢህአዴግና ተዋፅኦዊ አደረጃጀቱ</u>

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚደራጀው በሚከተለው ርእዮት አለም መሰረት ነው፡፡ ከአንድ ርእዮት አለም ወደሌላ ርእዮት አለም የመቀያየር መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወቅቱ የያዘውን ርእዮት አለም የሚከተሉ ግለሰቦች እየተቀላቀሉት ድርጅታዊ አቅሙና ግዝፈቱ እያደገ ይሄዳል፡፡ ምንም እንኳን ርእዮት አለሙን የማስፋትና የመተንተን እንዲሁም ጥልቀት የመስጠት ኃለፊነትና መብት የድርጅታዊ ልሂቁ ቢሆንም የፖለቲካ ፓርቲው ግን ግልፅ ያሉ መመርያዎችና መመልመያዎች ይኖሩታል፡፡

በተጨማሪም በድርጅቶች የሚፈጠር ህብረት ብዙ የተለያየ አወቃቀርና አደረጃት ሊኖረው ይችላል፡፡ ነፃ በሆኑ እና በርእዮት አለም ትስስር የሌላቸው ነገር ግን በአንዳንድ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚግባቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ መንገድ ህብረት የፈጠሩ ድርጅቶች የየራሳቸው ርእዮት አለም ስለሚከተሉ የአንደኛው ርእዮት አለም ከሌላኛው ፓርቲ ርእዮት አለም መገጣጠም አይጠበቅበትም፡፡ በሌላ በኩል ተመሳሳይ ርእዩት አለም የሚከተሉ ድርጅቶች ነገር ግን የተለያየ ብሄር ያለውን ህዝብ ለመወከል የሚታገሉ ድርጅቶች በተመሳሳይ መንገድ ህብረት ሊፈጥሩ ይችላሉ በነዚህ ተመሳሳይ ርእዮት አለም የሚያራምድ ድርጅቶች መካከል ያለው ልዮነት መሰረታዊ ያልሆነና በአካባቢያዊ ፖሊሲ ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ስለሆነም ህብረቱን የፈጠሩት አባል ድርጅቶችን የሚመሩ አካላት ህብረታቸው የሚከተለውን ርእዮት አለም በእኩል የማወቅ፣ የማስፋት ብሎም የመተንተን ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ህብረቱ ስትራተጂያዊእንዲሆንና ዘለቄታ እንዲኖረው ከተፈለገ እያንዳንዱ አባል ድርጅት አመራርየሚመለምልበት መስፈርት በምን ያክል ጥልቀት ድርጅቱ ብሎም ህብረቱን የሚመራበትን ርእዮት አለም ያውቀዋል፣ይተነትነዋል ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች (ፈተናዎች) በሚያጋጥሙበትወቅት ከዚህ ከሚከተለው ርእዮት አለም ተነስቶ መፍትሄ ያመጣል በዚህም የድርጅቱንም ሆነ የህብረቱን ፖለቲካዊ ህልውና ያረጋግጣል የሚል ይሆናል፡፡

አሁን ኢህአዴግን የመሰረቱ የፖለቲካ ድርጅቶች በርግጥስ የአንድ አይነት ርእዮት አለም ተከታዮች ናቸውን? ካልሆኑስ የየራሳቸው የሚያራምዱት ርእዮት አለም አላቸው?ወይንስ የአስተሳሰብ ጥገኞች እንዲሁም የስልጣንና የጥቅም እስረኞች ናቸው?

እነዚህን ጥያቄዎች ተገቢው ዝርዝር እይታ በማድረግ ሊመለሱ የሚገባቸው ናቸው፡፡

ኢህአዲግ አብዮታዊ ዴሞክራራን እንደርእዮት አለም የሚከተል የፖርቲዎች ህብረት (ግንባር) ነው ይህ ከሆነ እያንዳዱ አባል ድርጅት በዚህ ኢህአዴግ በሚከተለው ርእዮት አለም ጥርት ያለ እውቀት እና የመፈፀሙ፣ የማስፋቱ እንዲሁም ተመራምሮ የማሳደጉ ሃላፊነት አለባቸው ማለት ነው፡፡ የየድርጅቶቹ አመራሮችም በርእዩት አለሙ ዞርያ (የእውቀት መበላለጥ ቢኖርም) የመቀበሉ፣የማስፈፀሙ እንዲሁም የመተንተኑ አቅም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገር ግን በእውነታው ስናይ እንኳን ሌሎች አባል ድርጅቶች አመራሮች ይቅርና በህውሓት ውስጥ ያሉት አብዛኞዎቹ አመራሮች ይህን የሚመሩበትን ርእዮት አለም መተንተን፣ መመርመር ቀርቶ ማነብነብ የሚችሉ አይመስለኝም፡፡ በአንድ ወቅት የዛሚ 90.7 ራዲዮ ጣብያ የርእዮት አለም ክርክር ለማድረግ የተላያዮ ወገኖች ጠርቶ ነበር በሚገርም ሁኔታ ርእዮት አለሙን ለመግለፅ ያልመጣው ኢህአዴግ ብቻ ነበር፡፡ ምክንቱም ግልፅ ነው ኢህአዲግን አሁን እየመሩ ያሉት ግለሰቦች እንኳን በወከሉት ድርጅት ደረጃ አይደለም በግላቸውም አብዮታዊ ዴሞክራሲንና ይህ ርእዮት አለም ሊፈጥረው የሚፍጨረጨርለት ዲሞክራሲዊ ልማታዊ መንግስት አገናዘበው ትስስሩን መግለፅ አይችሉም፡፡

ስለዚህ ኢህአዴግን እንደ ግንባር የፈጠሩት ድርጅች በሚከተሉት በሚመሩበት ርእዮት አለም ላይ የተሟላ እውቀት ከሌላቸው እንደዚሁም የራሳቸው የሆነ ርእዮት አለም የማይከተሉ ከሆነ የፖለቲካ

ጥገኞች ናቸው ማለት ነው፡፡ ድርጅቶችን የሚመሩት አካላት ስልጣናቸውና ጥቅማቸው እስከተጠበቀ ድረስ ብቻ ነው የአህአዴግ አባልነታቸው የሚቆየው፡፡ ጥቅማችን ተነካ ስልጣናችን ተነካ ብለው ባሰቡበት ወቅት በሙሉ አቅማቸው በተናጠልም ይሁን በድርጅት ፀረ ርእዮት አለሙ ይዘምታሉ ኢህአዴግን ለማፍረስ ይረባረባሉ፡፡ የሰሩትን ወንጀል መሰረት ያደረገ የህግ ተጠያቂነት ሊያስከትልባቸው የሚችለው የሃይል ሚዛኑ ወደ ህውሓት ካዘነበለ ብቻ ከህብረቱ ሳይወጡ ሊቀጥሉ ይችላሉ ሚዛኑ ከህውሓት እጅ የወጣ ሲመስላቸው ህብረቱን አፍርሰው ይበተናሉ፡፡

ሰለሆነም ኢህአዴግ አሁን እየተከተለው ያለው የተዋፅኦ አደረጃጀት ርእዮት አለሙን ከሚያውቁት ከሚመረምሩትና ከሚተነትኑት አመራሮች ውስጥ ብሄራዊ ተዋፅኦ ያለው አደረጃጀት ቢከተል ተገቢም ትክክለኛም ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን ርእዮት አለሙን ከነጭራሹ ከማያውቁት ሰዎች እየመጣ ያለ ተዋፅኦዊ አደረጃጀት ከላይ ለማብራራት እንደሞከርኩት የሃይል ሚዛኑን እያየ የሚኖር የፖለቲካ አመራር ስለሚሆን ፀረ ኢህአዴግ የሚገነባው ስርዓት መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

## <u>ይቅር ወደ ህዝቡ ወደ አባል ድርጅት አመራሮች ያልተሸጋገረ ርእዮት አለም</u>

አንድ ርእዮተ አለም ከተውልድ ወደ ትውልድ መሸጋገር ካልቻለና በየወቅቱ እየተመረመረ ጥናት እየተደረገበት ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማጣጣም ካልተቻለ በአንድ ጊዜ ብልጭ በሎ የሚጠፋ አስተሳሰብ ይሆናል፡፡ ማንኛውም ዓይነት አስተሳሰብ የሚያራምድ ድርጅታዊ ልሂቅ የአስተሳሰቡን ቀጣይነት ለማረጋገጥ መሻሻል ያለበትን ለማሻሻል መጥራት ያለበትን ለማጥራት እንዲችል የተለያዮ ተቋማት ይከፍታል፡፡ በነዚህ ተቀዋማትም አማካኝነት የወደፊት የአስተሳሰቡ አራማጅባለ ተስፋዎችን ይኮተኩትበታ፡፡ ህውሓት በትጥቅ ትግሉ ወቅት በነበሩት የተለያዩ ተቋማት አማካኝነት ካድሬዎችን እያሰለጠነብቃት ያላቸውና ለወደፊቱ በአመራር ደረጃ ሊያስቀምጣቸው (ሊያበቃቸው) የሚችላቸውን ተተኪ አመራሮችን ያፈራ ነበር ወይንም ለማፍራት ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ ወደ ህውሓት አመራር ሊመጡ የሚችሉ በድርጅቱ ልሂቃን በየስብሰባው ይነገርላቸው ነበር የተቀረፁ (mentored leaders) እየተባሉ ጎልተው መታየት ይጀምሩ ነበር፡፡ ይህ አካሄድ በትንሹ የህውሓት በቀጣይ የማእከላዊ ኮሚቴ ገብተው የሙከራ እድል የሚሰጣቸው እነማን እንደሆኑ በአብዛኛው አባል ዘንድ አስቀድመው እንዲታወቁ እየተደረገ ይኬድ ነበር፡፡

ይህ አይነትን አካሄድ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በወቅቱ ካለው ትውልድ በላይ እንደሚቀጥል አመላካች አካሄድ ነው፡፡ በመቶ አመታት የሚቆጠር እድሜ ያላቸው የተለያዮ አገራት የፖለቲካ ፓርቲዎች እስከ አሁን ድረስ ህልውናቸው ሊቀጥል የቻለው ከትውልድ ትውልድ ቅብብሎሽ የሚያደርጉበት መዋቅራዊ አሰራር ስላላቸውና ዋናው የፖርቲውን አስተሳሰብ በጥናትና ምርምር እስደገፈው ከወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ጋር የሚያጣጥሙ አደረጃጀቶች ባለቤት በመሆናቸው ነው፡፡

ከ3ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ በኋላ አመራሩን የያዘው የህውሓት ልሂቅ እየተንገደገደ እስከ 1990ዎች አጋማሽ ካድሬ ለማስተማር ቢሞክርም በተለይ በ1993 ዓ/ም በኋላ የፖለቲካ ትምህርቱን አስተሳሰቡንም የማጥናት አዲስ ሃሳብ የማፍለቅም የመተቸትም ይሁን የማሻሻል መብቱን ለአንድ ሰው አስረክቦት ሰለነበረ ህውሓት/ኢህአዴግ የሚመራበት አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚተነትነው በአቶ መለስ ዜናዊ ነበር፤ የሚተቸውም እንደዛው የሚሻሻለውም በተመሳሳይ፡፡ በአቶ መለስ ዜናዊ ተጠቅልሎ የተያዘው የርእዮት አለም ፍተሸና ባቤትነት በተቋም እጅ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ርእዮት አለሙ ላይ ጥልቅ ምርምር እየተደረገና በጥልቀት ተመርምሮ የጠራውን አስተሳሰብ ወደ ተገቢው ስልጠና እየወረደ ብቃት ያለው እንዲሁም በአስተሳሰቡ ጥልቀት ያለውን አባል እየመለመለ እጩ አመራር የማውጣቱ ጉዳይ የነዚህ ምርመርና የስርፁት ተቋማት ስራ ሊሆን በቻለ ነበር፡፡ እነዚህ ተቋማትም አሁን ሲፈልግ የኢህአፓወይንም የኦነግ አመራር የነበረ ካበውን አውልቆ ምንም ዓይንት የአስተሳሰብና የርእዮት አለም ፈተና ሳይደረግለት በአንድ ሌሊት የኢህአዴግ አመራር እናት ላይ ፊጢጥ ብሎ አናገኘውም ነበር፡፡

ስለሆነም ኢህአዲግ በሚመራበት አብዮታዊ ዲሞክረሲ ርእዮት አለም ዙርያ አሁን በተለያዮ የሚኒስቴር መስራቤቶችን የሚመሩት ይቅርና የኢህአዴግ ፅ/ቤትን የሚመሩ ኃላፊዎችም የጠራ ግንዛቤ ያላቸው አይመስለኝ፡፡ ምክንያቱም በተቋም ሰልጥነውና ተመልምለው ያለፉሳይሆኑ አብዛኞቹ የብአዴን አመራሮች የእነ አቶ በረከተ ስምኦን እና አቶ አዲሱ ለገሰን ተከትለው ወይንም በነሱ ተመልምለው የመጡ ስለሆኑ፤በኦህዲድም በተመሳሳይ መንገድ አቶ አባዱላ ገመዳ ጋር ባላቸው ቅርበት ወደ ስልጣን የመጡ እንጂ መሆን በሚገባው መንገድ፣ ማለፍ የሚገባቸውን የስርፀትና ምርምር ደረጃዎቸን አልፈው የመጡ አይደሉም፡፡

በተለይ በህውሓት የከፋ የሚያደርገው በቀደምት የድርጅቱ ልሂቅ ተቋቁሞና አመራር እየመለመለ ይሄድበት የነበረን ትንሽ ተቋም አፍርሶ ከአቶ መለስ ዜናዊ የሚወጡትን ቃላት እየለቀሙ ማስተጋባት የሚችሉትን ብቻ መመልመል ላይ ያተኮረ አካሄድ ህውሓት አመራር (አቶ መለስ ዜናዊ) በአመራር ቀጣይነቱ ላይ በመቆመርራሱን በራሱ የማጥፋት ሂደት ውስጥ ነበር የገባው፡፡

ህውሓት ከዚህ ቀደም የነበረውን ተቋማዊ የማብቃት እንቅስቃሴ ተመልሶ የማግኘት እድሉ አለው፡፡ ይህን እድል መልሶ አግኝቶ የሚጠቀምበት ከሆነ አብዮታው ዴሞክራሲዊ ርእዮት አለሙ ሂወት ኖሮት እንዲቀጥል ተስፋ ሊኖረው ይችላላ፡፡ በተጨማሪም በኢህአዲግ ውስጥ እንደግንባር አመራር ደረጃ ላይ ያለውን አለመብቃት ሊያስተካክለው ይችላል፡፡ እንደኔ እምነት የህወሓት አመራር ይህን ለማድረግ እንዲችል ሁለት መሰረታዊ ተቋማትን በፍጥነት ማቋቋም ከቻለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ርእዮት አለም መቀጠል ብቻ ሳይሆን ተግባር ላይ ሊያውለው የሚታገልለትን ልማታዊ ዴሚክራሲያዊ መንግስታዊ አወቃቀር መሬት ላይ ወርዶ ተጨባጭ ለውጥ በህዝብ ልማት ላይ ሊያመጣ ይችላል፡፡

እነዚህ ተቋማትም፡-

1. ኢህአዴግ የሚከተለውን ርእዮት አለም እና ተዛማጅ መንግስታዊ መዋቅራዊ ጥናቶችን የሚደርግ የድርጅቱ የምርምርና ስርፀት ማእከል መመስረትና በተገቢ ሰዎች እንዲመራ ማድረግ አለበት፡፡ እዚህ ላይ መደረግ ያለበት የአቶ መለስ ዜናዊ ፅሁፎችን በቅጡ ያላነበቡና ካነበቡም የማያምኑበትን ሰዎች በመለሰ አካዳሚዎች እንደተቀመጡት ሆኖ የአስተሳሰቡ አራማጆችን ሳይሆን የአስተሳሰቡ አፍራሾችን የሚያፈሩ ተቋማት እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፤
2. ስርዓቱን የጠበቀ የምልመላ እና የማብቃት ሃላፊነት የሚወስድተቋም ማቋቋም፡፡ ሁሉም በስልጠናው ኮከብ የተባለ ብቁ መሪ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ ሰለሆነም መሪነት እየተኮተኮተ የሚያድግ መሆን አለበት፡፡ ወደ መሪነት ሲመጣ ሰፊ አስተሳሰብንና በብልሃት መምራትን (leadership wisdom) መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ መሪ ሲኮን የሚወክለውን አስተሳሰብ ብቻ ሳሆን የማይወክለውን አስተሳሰብ የሚያራምዱትንም ጭምር ነው የሚመራው፡፡ በዚህ መሰረት መሪ ማፍራት የሚችሉ ጠንካራ ተቋማት ያስፈልጋሉ፡፡

እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ተቋማት (ነብስ ያላቸው) የሌሉት ኢህአዴግ የወደፊት መሪዎችን ማፍራት በሚችልበት ቁመና ላይ አይደለም ያለው፡፡

ለማጠቃለል ኢህአዴግ አሁን ባለበት ሁኔታ እንኳን አስተሳሰቡን ወደ ህዝብ አውርዶ ሊያስርፅ ይቅርና የከፍተኛ አመራሩን እንኳን ማብቃት የሚችል አይደለም፡፡ ብዙዎቹ ከፍተኛ አመራሮቹ ከግንቦት 7 እና ከኦነግ ወይንም ኢህአዴግን ከሚቃወሙት ድርጅት መሪዎች ይብሱ እንደሆነ ነው እንጂ የሚሻሉ አይደሉም፡፡

<u>ብሄርና ብሄራዊማንነት በኢህአዴግ ባለስልጣናት</u>

በህገመንግስቱ መሰረት የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች የኢትዮጵያ ብሄርና ብሄረሰቦች ናቸው፡፡ የኢትዮጲያ ብሄርና ብሄረሰቦች እንደማንኛውም በአለም ላይ የሚኖሩ ህዝቦች የየራሳቸው ቋንቋ፣ ባህል፣ ስነልቦና እንዲሁም ኩታገጠም ስነምድራዊ አሰፋፈር ያላቸው ህዝቦች በኢኮኖሚ ተሳሰረው የሚፈጥሩት ማንነት ነው፡፡ ኢትዮጲያ የበርካታ ብሄርና ብሄረሰቦች አገር ናት እነዚህ ብሄርና ብሄረሰቦች በዝርዝር በስነህዝብ ሙሁራን (social anthropologists) መጠናት ያለበት ቢሆንም እርስ በርሳቸው የሚያስተሳስሯቸው በርካታ ባህላዊና፣ ታርካዊ እና የአኗኗር እሴቶች ያሏቸው ህዝቦች ናቸው፡፡ ከዚህ መተሳሰረ በተነሳም አጎራባች ከሆኑ ብሄሮችና ብሄረሰቦች በዘለለ በመላው አገር የሚገኙ የተለያዮ ብሄርና ብሄረሰቦች ተጋብተውና ተዋልደው የሚኖሩባት የህዝቦች መስተጋብር የሚታይበት ሃገር ናት፡፡

በመሰረታዊ ትንታኔው ብሄር ማለት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ፣አንድ ቋንቋ የሚናገሩ፣ተመሳሳይ ስነልቦና ያላቸው ሰዎች የፈጠሩት ፖለቲካዊ ጥምረት ወይንም መስተጋብር ነው፡፡ ብሄርና ብሄረሰብ በዚህ በገለፅኩት መንገድ የሚገለፁ የሰዎች ስብስብ ከሆኑ እነዚህ የመሰባሰቢያ መስፈርቶች

በማንኛውም ወቅት ሊያዙ (ሊወረሱ) የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በትግራይ ተወልዶ ወለጋ ሄዶ ቢያድግና፣ቢማር፣ረዘም ላለ ጊዜ ከማበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ቢኖር፡-

- የማህበረሰቡን ቋንቋ ማለትም ኦሮምኛን ይማራል፣ይናገራል
- ከማህረሰቡ ጋር የቀን ተቀን ባህላዊና ህዝባዊ መስተጋብሮች ውስጥ እየተሳተፈ ከአንድ የወለጋ ኦሮሞ ሰው የሚጠበቀውን ማህራዊ ግዴታዎችንና ተግባራትን ቢፈፅም ከማህረሰቡ ጋር የሚኖረው ስነልቦናዊ ቁርኝት እየጨመረ ይሄዳል ህብረተሰቡን በቅጡ፣ በስርዓቱ ይረዳዋል ራሱን ያዋህዳል ህብረተሰቡም በማኛውም ማህራዊና ባህላዊ ኩነቶች ያለ ልዩነት ያሳትፈዋል፡፡

ስለሆነም በዚህ ባልኩት ወለጋ ውስጥ የሚኖረው ነገር ግን በትግራይ የተወለደው ሰው ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ትስስሩ ከላይ በገለፅኳቸው መንገድ ከተወለደበት ከትግራይ ይልቅ የበለጠ ስነልቦናዊ ትስስር ከማህረሰቡ ጋር መፍጠር የሚችለው በወለጋ ነው፡፡

ይህ ሰው በፖለቲካዊ መመዘኛ ኦሮሞ ነው፡፡ ሊግባባም የተቀላጠፈ ስረመሰረት ያለው ተግባሮት ሊኖረው የሚችልም ከኦሮሞ ማህበረሰብ ጋር እንጂ ከትግራይ ጋር አይደለም፡፡ ወደ ትግራይ ተወስዶ መልሶ እንዲቋቋም ለማድረግ ቢሞከር ባህሉን ቋንቋውን ስነልቦናውን እንደ አዲስ መማር አለበት፡፡ እንደ አዲስ ተምሮ የትግራይን ህዝብ ስነልቦና ቋንቋ ባህል ችሎ ማህበረሰቡን ከመሰለ አሁንም ይህ ሰው ትግራዋይ ይሆናል፡፡

ስለዚህ ብሄር ማለት በማንኛውም ወቅት የሚወርስ ከማህበረሰባዊ ትስስርና ስነልቦናዊ እንዲሁም በመሰረቱ በግለሰቡ ውሳኔ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ማንነት ነው፡፡ ብሄር እና ብሄረሰባዊነት በማንኛውም ጊዜ ዜጎች ከአኗኗራቸው ወይንም ከማህበረሰቡ ጋር በትስስር ከፈጠሩት ስነልቦና ጋር በተገናኘ ለእያንዳንዳቸው የመምረጥ መብት መተው ያለበት የማንነት ውሳኔ ነው፡፡

ብሄር ከዘረመል (DNA) ጋር ምን ዓይነት ግኑኝነት የለውም አንድ ሰው አባቱ አማራ ስለሆነ ወይም እናቱ ትግራይ ስለሆነች ከአባቱ ወይን ከእናቱ የሚወርሰው ማንነት አይደለም፡፡ በዚህ እሳቤ ከተሄደ አለም ላይ አንድም ከዚህ ብቻ የተፈጠረ ተብሎ አንዳንዶች እንደሚሉት ንፁህ ዘር የሚባል አለም ላይ የለም ሊኖርም አይችልም፡፡

በአንድ ወቅት በአሜሪካ የKKK መሪ የዘረመል (DNA) ምርመራ በማድረግ የዘር ሀረጉን ለማወቅ ተስማምቶ ምርምራ አደረገ ፣ በነገራችን ላይ KKK ነጭ እና ጥቁር በጭራሽ መነካካት የለበትም ውሃና ዘይት እንደማይቀላቀል ሁሉ ነጭ እና ጥቁር በምንም ተአምር በዘር መቀላቀል የለበት እና ነጮች ከጥቁሮች የበለጠ፣ የተሸለ ንፁህ ዘር ስላለን እንዲደባለቅብን አንፈልግም ብለው የሚያምኑ የነጭ የበላይነት የሚሰብኩ እጅግ ዘረኛ የሚባሉ የነጮች ስብስብ ነው፡፡ የዚህ ግለሰብ የዘረመል ምርመራ ውጤት በቀጥታ የሚተላለፍ የቴሌቪዥን ስርጭት ላይ ነበር የተከፈተው በውጤቱም መሰረት ሰውየው 86% ነጭ ካውካዢያን ሲሆን 14% ግን የከሰሃራ በታች ጥቁር አፍሪካዊ ነበር፡፡ ከዚህ ታሪክ የምንረዳው ነገር ቢኖር እንኳን በመልክአ ምድራዊ አሰፋፈርና በባህላዊ ትስስር የጠበቀ

ቁርኝነት ያለንና ተሳስረን የምንኖር ኢትዮጲያውያን ብሄርና ብሄረሰቦች፤ በፍፁም የሚያገናኘን የዘር ትስስር የለንም የሚሉቱም ሳይቀሩ ተቀላቅለው ነው የሚኖሩት፡፡

ስለሆነም ሰዎችን በዘረመል ለመለየት እና ብሄርን ይሁን ብሄረሰብን ከዘረመል ጋር አገናኝቶ ፖለቲካዊ ለማድረግ መሞከር እጅግ ድንቁርና ከመሆኑም በዘለለ ኢ-ሳይንሳዊም ጭምር ነው፡፡

በአንድ ወቅት በአገራችን ፖለቲካ ትልቅ ቦታ ያላቸው ሚኒስቴር በማህበራዊ ሚድያ ገብተው አያትዎ ትግሬ ናቸው ስለዚህ እርሶ ትግሬ ኖት ኦሮሞ አይደሉም ተብለው ሲጠየቁ የመለሱት መልስ የአገራችን ፖለቲከኞች ያራሳቸውን ህገመንግስት እንደማያውቁት የሚያሳይ ነበር፡፡ መልሳቸውም “አባቴ በሄወት ቢኖር ኖሮና ቢጠየቅደስ ይለኝ ነበር” የሚል ነበር፡፡ ነገር ግን የብሄር ማንነት ጉዳይ የእሳቸው ጉዳይ እንጂ የአባታቸው ወይንም የእናታቸው ጉዳይ ሊሆን እደማይችል ከላይ በገለፅኩት አመክንዮ መልሳቸው የወረደ ነው ባይ ነኝ፡፡

አብዛኞች የኢህአዴግ ባለስልጣናት ብሄርን ከዘር ሀረግ (DNA) ጋር በማገናኘት ነው የሚተነትኑትም ወይንም የሚመለከቱት፡፡ ባለፉት 26 ዓመታት በህገመንግስቱ ላይ የሰፈረውን ብሄር ብሄረሰብ በተመለከተ ያለውንና የተቀመጠውን ህጋዊና ፖለቲካዊ ትንታኔ እንኳን በቅጡ የተረዱት አይመስሉም የተረዱት ከሆኑ ደግሞ ሆን ብለው ለፖለቲካዊ መጠቀሚያቸው ለማድረግና የሙስና ተግባራቸው መሸፈኛ እንዲሆን እጅግ ዘረኛ በሆነ መንገድ ይጠቀሙበታል እንጂ በትክክለኛው መንገድ እየወሰዱት አይደለም፡፡

ለማጠቃለል በኢትዮጲያ ብሄር ወይም ብሄረሰብ ማለት ፖለቲካዊ ማንነት እንጂ የዘር ሀረግ/ዘር (Genealogical) አይደለም፡፡

<u>ሕግና ስርአት ማስከበር ቀዳሚ የኢህአዴግ መራሹ መንግስት ብቸኛውመንገድ ስለመሆኑ</u>

<u>........ይቀጥላል</u>

<u>የሃገር ሽማገሌዎች ፓርላማ ስለማቋቋምና ሃገር በቀል የግጭት ማስወገድ አቅምን መጠቀም</u>

<u>...... ይቀጥላል</u>